# የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች

## ድነት፣መከራ፣ቅድስና፣ደስታ፣ሕያው ተስፋ

(ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተዘጋጀ)

**(የኢትዮጵያውያን ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤ/ክ)**

**ዳላስ**

**ቅዱሳንን የማጽናት አገልግሎት**


Ethiopian Evangelical Baptist Church

2822 S Jupiter Rd, Garland TX 75041

**www.wongelkedallas.org**
**www.eebc-dallas.org**
**Tel.2147030100**
**Fax 2147030161**


Sept 2012

# አንደኛ የጴጥሮስ መልእክት

## መግቢያ

የአንደኛ ጴጥሮስ መልእክት መልእክት ጸሐፊ ከ12ቱ የጌታ ደቀ መዛሙርት ወይም ሐዋርያት አንዱ ሲሆን የአይሁድ መጠሪያ ስሙ ስምዖን ይባል ነበር (ማቴ 10፡1-2)። የአረማይክ ስሙም ኬፋ  ይባል ነበር። በሙያውም ዓሳ አጥማጅና ያልተማረ የተባለ ሰው (ሐዋ 4፡13)። በባሕሪይውም  ፈጣንና ቶሎ ቶሎ የሚቀያየር ደቀ መዝሙር ነው። ክርስቶስንም  በምድር በተከተለበት ወቅት በብዙ ዓይነት ሰዎች ፊት ጌታን የካደና ተመልሶም ንሰሃ የገባ የክርስቶስ ተከታይ ነበር (ማቴ 26፡17-75)።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንደሚነግረን ጴጥሮስ ከጌታ ትንሳኤና እርገት በኋላ በህይወቱ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲመጣ ራሱን ለወንጌል የሰጠ ከፊት ገጽ የሚገኝ ሐዋርያ ነው (ሐዋ ከ1-12 ምዕራፎች)። ከዚያም ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ከሌሎችም ጋር በወንጌል አገልግሎት ህይወቱን ለወንጌል የሰጠ ሐዋርያ ነበር (ሐዋ 15 ይመልከቱ) ።

በስሙ የተጻፈ ወንጌል ባይኖርም ከማርቆስ ወንጌል ጀርባም ሐዋርያ ጴጥሮስ ትልቅ ሚና እንዳለው ይታመናል (አመልካች ጥቅሶች ሐዋ 12፡12፣1ጴጥ 5፡13) ። ማርቆስ ከጌታ ከ12ቱ ደቀ መዛሙርቱ አንዱ አልነበረም። ስለዚህ ማርቆስ እንደ ዓይን ምስክር ከሐዋርያ ጴጥሮስ መረጃ እንደተቀበለ ብዙዎች ይስማማሉ።

ጴጥሮስ በጌታ ስላለው እምነቱ በስቅላት እንደተሰዋም ይነገራል። የጌታን ጸጋ በሐዋርያው ጴጥሮስ  በህይወቱ ምን ያህል ታላቅ መሆኑን ማየትና ማስተዋል አይከብድም።

አንደኛ የጴጥሮስ መልዕክት የተጻፈውም ከ64-65 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ተብሎ ይታወቃል። ይህ መልእክት የተጻፈው ዛሬ ቱርክ ተብላ በምትታወቀው በሰሜናዊ ትንሹ እስያ አከባቢ ለነበሩ አምስት ሀገሮች (በጳንጦስና በገላትያ በቀጳዶቅያም በእስያም በቢታንያም) ስለ ክርስትና መከራና ስደት ውስጥ ለነበሩ ለአይሁድና ለአህዛብ ክርስቲያኖች ነው። ክርስቲያኖች በእነዚህ አምስቱ ሀገሮች ተበትነው ይኖሩ ነበር (Diaspora):: እነዚህ አማኞች በብዙ አቅጣጫ ስለ ክርስትና በብዙ መከራ ውስጥ እያለፉ የነበሩ እንደሆነ መልእክቱ ይነግረናል “ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል” (1ጴጥ 1፡7)።

አንደኛ የጴጥሮስ መልእክት አምስት ምዕራፎች ሲኖሩት ከሰባቱ አጠቃላይ መልእክቶች (General Epistles) ከተባሉት አንዱ ነው:: እነዚህም አጠቃላይ መልዕክቶች የሚባሉት የያዕቆብ፣ሁለቱ የጴጥሮስ፣ ሶስቱ የዮሐንስ እና የይሁዳ መልእክቶች ናቸው። እነዚህ መልክቶች ለአንድ ውስን ቤተ ክርስቲያን የተጻፉ አይደሉም። አጠቃላይ መልዕክቶች የተጻፉት ዓላማቸው በተለይም ለሁለት ነገሮች ይሆናል 1) ልዩ ልዩ መከራ የበዛባቸውን አማኞች ተስፋ እንዳላቸው ለማሳወቅና ለማጽናት 2) እውነተኛውን የክርስትና ትምህርት በማሳወቅ የሀሰት ትምህርትን መቃወም።

አንዳንዶች አንደኛ የጴጥሮስ መልዕክት የተጻፈው ባቢሎን ተብሎ ከሚጠራ ከሰሜናው ግብጽ፣ከባቢሎን (ከዛሬው ኢራቅ) ወይም በምሳሌያዊ ንግግር ከሮሜ ከተማ ተብሎ ይታመናል ((ራዕይ 17፥5, 18፥2 18፥10፣ 18፥21) ። ሮም በጊዜው ስለምትፈራ በምሳሌ ባቢሎን ትባል ነበር ይባላል። ከሮም ከተማ ተጻፈ የሚባለው የመጀመሪያውን ቦታ ይይዛል፤ ምክንያቱም ሐዋርያዊ ጴጥሮስ በሮሜ ታስሮ ከሁለት ዓመት በኋላ ከ66-67 ዓ/ም ተዘቅዝቆ ተሰቅሎ እንደተሰዋ ታሪክ ያምናል።

የአንደኛ ጴጥሮስ መልእክት ዋና ዓላማ ክርስቶስን ያመኑ አማኞች ስለ ክርስትና እውነትና በክርስቶስ ስላለው ህያው ተስፋ ለሚገጥሙት ጥላቻዎችና መከራዎች እንዴት መመለስና መመላለስ እንዳለበት በጥብቅ ያስተምራል። 1ጴጥ 1፡6፣7፣ 2፡12 እና 3፡17 ስለ መከራዎቹ ዓይነቶች ይናገራል። “በመከራ ውስጥ መጽናት እንዴት ይቻላል?” ለሚል ጥያቄም መልስ መስጠት ዋናው ነገር ነው።

የ1ጴጥሮስ መልእክት ጥናት ሲዘጋጅ ዋናው ዓላማ የክርስቶስን ፍለጋ በመከተል በቤተክርስቲያናችን እያንዳንዳችን ለክርስትና የምንከፍለው ዋጋ አሁንም ይሁን በመጨረሻ የማይገመት ተስፋ፣ደስታና ክብር እንዳላው ማሳየት ነው። ስለዚህ ጌታ እስኪመጣ እስከ መጨረሻ ድረስ በማንኛውም ዓይነት መከራዎች እንጽና። ጌታ ሲመጣ ሁሉም ዓይነት መከራ ያበቃል።

ቅዱሳንን የማጽናት አገልግሎት

በዚህ ጥናት ማንኛውም ዓይነት ግልጽ ያልሆነ ነገር ቢኖር ከዚህ በታች ባለው ስልክ ደውለው ይጠይቁን

214 703 0100 (ቢሮ) 972 375 8897 (የእጅ)

EMAIL getachew_habte@yahoo.com

## ጥናት አንድ
## የጸሎትና የመግቢያ ጥያቄዎች ጥናት ቀን

1. ከመግቢያ ስለ ጴጥሮስ ህይወት ምን ተማራችሁ? ደካማና ጠንካራ ጎኑን ተነጋገሩ (ከዚህ በሰፋ መልኩ ማንኛውንም እውነት ያለበትን ነገር ስለ ጴጥሮስ ህይወት መነጋገር ትችላላችሁ)
2. ከመግቢያ ስለ ጴጥሮስ መልዕክትስ ምን ተረዳችሁ? ጠቅላላ የጥናቱ ዓላማስ ምንድ ነው?
3. ዛሬ ከጴጥሮስ ህይወትና አገልግሎት ከመግቢያ ምን ተማርን

# ጥናት ሁለት
# 1ኛ ጴጥ 1፡1-12
## የክርስቲያን ድነት እና የቅድስና ኑሮ

**ዓላማ፡-** የሕብረቱ ተሳታፊዎች የድነታቸውን ታላቅነት ተረድተው፣ ይህን ድነት የሚመጥን የቅድስና ኑሮ ለመኖር እንዲወስኑ መርዳት

**መግቢያ፡-** ለአገር መሪ ሥራውን ትቶ ከሥራ ፈት መንደር ሰዎች ጋር መዋል የማይመጥን እና ተገቢ ያልሆነ ነገር ነው። ልክ እንዲሁ ለአማኝ የተጠራለትን እና የተጠራበትን ድነት ዘንግቶ ኑሮው እንደ ዓለምና ሥጋ ምኞት ከሆነ የማይመጥነውን ኑሮ እየኖረ ነው ማለት ነው። 1ኛ ጴጥ 1 ይህንን እውነት በሚገባ የሚያስገነዝብ ምዕራፍ ነው። ሐዋርያው በመጀመሪያው 12 ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሔር በክርስቶስ አምነው ለዳኑት በክርስቶስ ኢየሱስ መገለጥ ጊዜ ያዘጋጀላቸውን መዳን እና ይህ ድነት ያስገኘልንን ደስታ ይተነትናል። ቀጥሎ ባሉት ቁጥሮች  ግን ይህንን ድነት የተቀበሉት አማኞች ሊኖሩት እና ሊለማመዱት የሚገባውን የቅድስና ኖሮ ያሳስባል። በዛሬው ጥናታችን የክርስቲያን ድነት ምን እንደሚመስል እና ይህንን የሚመጥነውን የቅድስና ኑሮ እናጠናለን።

## የክርስቲያን ድነት 1ጴጥሮስ 1፡1-12

### 1. የድነት ዕቅድ ና መጻተኝነት 1ጴጥሮስ 1፡1-2

በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች ሐዋሪያው ራሱን እና የመልዕክቱን ተቀባዮች አስተዋውቆ ሰላምታውን ያቀርባል። የአማኞቹን ማንነት ሲያስተዋውቅ እግረ መንገዱን የአማኖች ድነት አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ እና የታቀደ እንደሆነ ነገር ግን በክርስቶስ ደም ተረጭተው ይድኑና ለክርስቶስ ይታዘዙ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ አሰራር የዳኑ መሆናቸውን ያሳስባል። በተጨማሪ በነዚህ ሁለት ቁጥሮች በመግቢያ እንደተጠቀሰው መልዕክቱ የተላከበትን ሀገሮች ከተናገረ በኋላ ተቀባዮቹን   **"ለተበተኑ መጻተኞች"፤"** ይህ ሀሳብ የሚያመለክተው አንዳንዶች አይሁድን ብቻነው በማለት ቢጽፉም  ብዙዎች የሚስማሙበት ግን በምድር ላይ

እንግዳ ሆነው ተበትነው የሚኖሩትን የአህዛብንም ሆነ የአይሁድን ክርስቲያኖችንን ያመለክታል። **“በእንግድነታችሁ ዘመን (1፡17)” የሚልም ሀሳብ ይህንኑ ይደግፋል።**

ከሰላምታው በመቀጠል በሚከተሉት 10 ቁጥሮች ውስጥ ቅዱስ ጴጥሮስ የአማኞችን ድነት እና በሱ የሚገኘውን ደስታ ያወሳል።

## 2. አማኝ የዳነው ለሕያው ተስፋ እና ለዘላለማዊ ለርስት ነው (1ጴጥሮስ 1፡3-5)

በዚህ ክፍል እንደሚነበበው አማኝ በክርስቶስ ዳግም የተወለደ አዲስ ፍጥረት መሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም ግን ጴጥሮስ አንደሚያስረዳው ዳግም የተወለደ አማኝ የዳነው ለሕያው ተስፋ እና ለማይጠፋ ርስት ነው። አማኝ የተሰጠው ተስፋ የውሸት ወይንም ዋጋ የሌለው አይደለም- ነገር ግን አንድ ቀን እውነት ሆኖ የሚገለጥ ነው። ይህም ተስፋ ጌታ ዳግም ሲገለጥ እያንዳንዱ በሚሰጠው ርስት ይረጋገጣል። ይህ ለአማኞች የታቀደው ርስት ምድራዊ አይደለም፣ አያረጅም፣ አይጠፋም እንዲሁም እንከን አይወጣለትም - ነገር ግን ሰማያዊ ነው፣ ዘላለማዊ ነው እንዲሁም ፍጹም ነው!

ነገር ግን ይህ ርስት “በመጨርሻ ዘመን” የሚገለጠውን መዳን ለሚያገኙ የተቀመጠ ነው። አማኝ በአንድ በኩል በክርስቶስ ኢየሱስ መዳኑ ግልጽ ቢሆንም፣ ግን የአማኝ ድነት የሚጠናቀቀው በመጨረሻው ዘመን በክርስቶስ ኢየሱስ መገለጥ ነው። ድነት ክርስቶስን በመማመን ቢጀምርም፣ በየእለት ኑሮአችን የሚቀጥል፣ እና በክርስቶስ መገለጥ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ተለውጠን ክርስቶስን በመምሰል የሚጠናቀቅ ነው። እንግዲህ ይህ ርስት እና ተስፋ በጌታ መገለጥ ጊዜ የሚገኘውን ድነት እንዲቀበሉ በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቁ አማኞች የተቀመጠ ነው!

## 3. ይህ ድነት በጊዜያዊ ሀዘን ውስጥም እንኳን ሐሤት የሚያስሞላ ነው (1ጴጥሮስ 1፡6-9)

ይህ መልዕክት የተጻፈላቸው አማኞች በጊዜው ይህ ነው በማይባል ከባድ መከራ ውስጥ እያለፉ የነበሩ ቢሆንም፣ ዳግም በመወለዳቸው የሚጠብቃቸውን ተስፋ ብቻ በማወቅ በብዙ ሐሤት የሚመላለሱ ነበሩ። በም 4፡12 ላይ በግልጽ

እንደሚያሳየው አማኞቹ “እንደ እሳት” የሚፈትን መከራ ውስጥ እያለፉ የነበሩ ናቸው። ሆኖም ግን መከራው ጊዜያዊ ነው ደግሞም አላማው እነሱን ለማጥራት እና ለበለጠ ክብር ለማብቃት በመሆኑ፣ በጊዜያው ፈተና ለጊዜው ቢያዝኑም ግን የድነቱ ደስታ በልጦባቸው “በማይነገር እና ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ” ተሰኝተዋል። የሚያልፉበት ፈተናዎች ደግሞ ከፖለቲካ፣ከሃይማኖት፣ከባህል፣ከማህበራዊ ኑሮ፣ በየቀኑ ከሚኖሩት የጽድቅ ኑሮ ተቃራን ነው። ከቤት ውስጥ ጀምሮ የክርስትና ኑሮ ማለትም ለጽድቅ መኖር መከራ ሊኖርበት ይችላል።

ዛሬም እንዲሁ አማኝ የሚያልፍበት ጊዜያዊ ሀዘን፣ መከራ እና ችግር ሊኖር እንዲሚችል አይካድም። ሆኖም ግን ይህ መከራ ጊዜያዊ መሆኑን እንዲሁም ዓላማውም አማኝን ይበልጥ ለማጠንከር እንደሆነ መረዳት አለብን። ማንኛውም መከራ ግን ለጽድቅ መሆን አለበት።

4. **የድነት ታላቅነት፡- ይህ ድነት ጥንት በነቢያት የተነገረ፣ መላዕክትም እንኳ ሊረዱት የሚሹት እውነት ነው (10-12)**

ይህ ለአማኞች የታሰበው በረከት እና ጸጋ፣ አዲስ መጤ የሆነ እንግዳ ትምህርት ሳይሆን በነቢያት አፍ ደጋግሞ የተነገረ እንዲሁም በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት የሰፈረ እውነት ነው። በጊዜው የተናገሩት ነቢያት ሙሉውን እውነት ለራሳቸው ባይረዱትም ቅሉ፣ ያስተላለፉት መልዕክት ግን ስለ ክርስቶስ እና በእርሱ ስለሚገኘው ድነት እና በረከት እንደሆነ ተረድተዋል።

ይህ የአማኞች ድነት በነቢያት የተነገረ ብቻ ሳይሆን ዛሬ መላዕክት ሳይቀሩ ሊረዱት የሚሹት እውነት ነው። እንዴ በኃጢአት ጠፍቶ የነበረው ሰው፣ በክርስቶስ ድኖ ለከበረ ነገር መታጨቱ፣ ለመላዕክት አስገራሚ እና ሊመለከቱት /ሊረዱት የሚሹት ነው።እንግዲህ የአማኝ ድነት ድንቅ ነገር ነው። ኃጢአተኛውን ውድ በሆነው የክርስቶስ ደም አጥቦ ማንጻቱ አልፎም ለከበረ ተስፋ እና ርስት ማጨቱ ያስገርማል። ግን ይህንን ድነት የተቀበለው አማኝ ከድነት በኋላ እንዴት ሊኖር ይገባል ለሚለው ጥያቄ ሐዋሪያው ጴጥሮስ ከቁ 13-25 ባለው በአምስት ነጥቦች መልስ ይሰጣል። ይህም በሚቀጥለው ጥናት የሚጠና ይሆናል።

***መደምደሚያ፡-***

በጌታ የዳነ አማኝ ለሕያው ተስፋ እና ለዘላለማዊ ርስት የተጠራ መሆኑን እርግጠኛ መሆን አለበት (1፡3-5)። ይህ ድነት በጊዜያዊ ሀዘን ውስጥም እንኳን ሐሤት የሚያስሞላ ነው (1፡6-9)። ይህ ድነት ጥንት በነቢያት የተነገረ፣ መላዕክትም እንኳ ሊረዱት የሚሹት እውነት ነው ። አማኝ ከማይጠፋ ዘር መወለዱ ከምንም ጋር ማነጻጸር አይቻልም። ለዚህም የተቀደሰ ኑሮ መኖር አለበት።

## *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በ1ጴጥሮስ 1፡1-2 መሰረት መልዕክቱ የተጻፈላቸው አማኞች የት ነበር ይኖሮ የነበሩ፤ምን ብሎስ ይጠራቸዋል? ለምን?
2. 1ጴጥሮስ 1፡1-5 በማንበብ ለአማኖች ስለ ተዘጋጀላቸው ህያው ተስፋና ዘላለማዊ ርስት ምንነት ተወያዩ? ለማን ነው ይህ ርስት የተቀመጠው? የነዚህ ወራሾችስ ባህርይ ምንድ ነው (ቁ.1 እና 2)?
3. 1ጴጥሮስ 1፡6-9 ስናነብ፤ ይህ ድነት በጊዜያዊ ሀዘን ውስጥ ደስታ ይጠይቃል? በዚህ ክፍል **"በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል"** ይላል። በልዩ ልዩ ፈተና ምንድ ነው? ይህን ጥያቄ መመለስ ለጴጥሮስ መልዕክት ጥናት መሰረታዊ ነገር ነው።
4. ሐዋሪያው ጴጥሮስ መከራ የተቀበለበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ካለ ጠቅሳችሁ ተነጋገሩ (ምናልባት ሐዋ 12፡1-12 ሌሎችንም ማየት ትችላላችሁ)?
5. በ1ጴጥሮስ 1፡10-12 የድነት ታላቅነት እንዴት ነው የተገለጠው? እንደዚህ አስባችሁ ታውቃላችሁ?
6. ከዛሬ ጥናት ምን ተማርኩ? እድል ስጡኝ ላካፍላችሁ! (ጊዜ ከበቃችሁና ከቻላችሁ ቀጥሎ ያለውን መዝሙር መዘመር ለጥናቱ ድጋፍ ይሆናል)

ምስጋና /2/ ለየሱስ ምስጋና

ይገባሃል አምላክ ላንተ፣

ለሆንከው ገናና

1. መከራም እንደሚያልፍ የጊዜውም ሀዘን

እንደምንራመድ ሁሉን ነገር አልፈን

ለቅሶ በዝማሬ ሀዘን በደስታ

እንደሚለወጡ ተነግሯል ያ ጌታ

2.እንደበደላችን አልተከፈለንም

ጌታ በመአቱ አልተገናኘንም

ምረትን የሚወድ የሰራዊት ጌታ

እዳዬን ለመክፈል በውርደት ተመታ

3.በኑሮዬ ሁሉ አንተን አስከብሬ

በመከራ ልለፍ ካንተ ጋራብሬ

የህይወት እስትንፋስ ሰተኸኛልና

መስዋዕቴ ይኸው ከነፍሴ ምስጋና

## ጥናት ሶስት

## 1ጴጥሮስ 1፡13-25 የቅድስና ኑሮ

**ዓላማ፡-** ክርስቲያን በመከራ ውስጥም ቢሆን ለእግዚአብሔር የተለየ ወይም የተቀደሰ ህይወት መኖር እንዳለበት ማሳወቅ።

***መግቢያ፡-*** "በእንግድነት ዘመን" ክርስቲያን እንዴት መኖር የሚል ትምህርት የዚህ ጥናት ዋና መሰረት ነው። አማኝ መሻቱ ወደ ፊት የሚጠብቀው ድነት ሊሆን እንደሆነ አውቆ ለዚህ ዓለም እንግዳ መሆኑን በየቀኑ ማሰላሰል አለበት። አማኝ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ እንዲሆን ተጠርቷል (1ጴጥ 1፡15-16)፣ በተጨማሪም የሚፈርድ እግዚአብሔር እንዳለ በማወቅ ሊመላለስ ይገባል ምክንያቱም አማኝ የተዋጀበት ዋጋ ውድ መሆኑን በማወቅ በቅድስናና በጽድቅ ሊኖር ይገባል። የዚህም መገለጫ በእውነተኛ ፍቅር መላለስ መሆኑን ይህ ጥናት ያሳውቃል።

### 1. አማኝ መሻቱ ወደ ፊት የሚጠብቀው ድነት ሊሆን ይገባል (1ጴጥሮስ 1፡13-14)

የዳነ አማኝ ተመልሶ ያለፈውን የአለማዊነት እና የስጋዊ ምኞትን እያስተናገደ ሊኖር አይገባም። ነገር ግን ራሱን አዘጋጅቶ ለስራ እንደተነሳ ገበሬ ወይንም ወታደር "የልቡናውን ወገብ ታጥቆ" በሙሉ ልቡ የሰማዩን እንዲሻ ተጠርቷል። "እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ"(ቆላ 3፡1) - ለዚህ ነው ጴጥሮስ **"አስቀድማችሁ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ"** ያለው።

### 2. አማኝ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ እንዲሆን ተጠርቷል (1ጴጥሮስ 1፡15-16)

እንደ አማኝ የቅድስና ኑሮ ልንኖር የሚገባን ስለዳንን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነም ነው። አማኝ የዳነው ክርስቶስን ለመምሰል ነው (ማቴ 5፡48)። መቀደስ ማለት መለየት ማለት ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር ቅዱስ ከሆነ ልጆቹም ቅዱሳን እንዲሆኑ ይገባል። ስለዚህ የዳነ አማኝ እንዴት ይመላለስ

ለሚለው ጥያቄ ሌላኛው መልስ እንደ እግዚአብሔር ቅድስናን በመላበስ የሚለው ይሆናል።

### 3. አማኝ የሚፈርድ እግዚአብሔር እንዳለ በማወቅ ሊመላለስ ይገባል (1ጴጥሮስ 1፡17-18)

በጌታ የዳነ አማኝ የዳነበትን ዋጋ ቢረሳ፣ የዓለም ፍቅር እየባሰበት ቢወድቅ፣ ሌላው ሊያስታውስ የሚገባው ነገር ግን "ለእያንዳንዱ እንደሥራው የሚፈርድ" ወይንም ዋጋ የሚሰጥ እግዚአብሔር መኖሩን ነው። በፍቅር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ላቃተው በቅጣት ደግሞ እንዲኖር ይገደዳል - ስለዚህ የሚቀጣ አባት መኖሩን በማወቅ እግዚአብሔርን በመፍራት አማኝ ሊኖር ይገባል።

### 4. አማኝ የተዋጀበት ዋጋ ውድ መሆኑን በማወቅ በቅድስና ሊኖር ይገባል (1ጴጥሮስ 1፡19-21)

አማኝ የዳነው በዚህ ምድር ላይ የከበሩ ነገሮች በሚያስከፍሉ ዋጋ ሳይሆን "በክቡር የክርስቶስ ደም" ነው። ድነት በምድራዊ ነገሮች ዋጋ ቢሆን ኖሮ አማኝ አለማዊ እና ምድራዊ በሆነ ነገር ተጠምዶ ለመኖር በቂ ምክንያት በኖረው ነበር። ሆኖም ግን አማኝ የዳነው ወደር በሌለው የክርስቶስ ደም ነው። ወይንም በሌላ አባባል የቅድስና ኑሮ እንዲኖር ከአለም እና ከኃጢአት የተዋጀው በክርስቶስ ደም ነው።

### 5. አማኝ በእውነተኛ ፍቅር ሊመላለስ ይገባል (1ጴጥሮስ 1፡22-25)።

በመጨርሻም ክርስቲያኖች ከሌሎች አማኞች ጋር በሚኖረው ግንኙነት እውነተኛ በሆነ ፍቅር እንዲመላለሱ ተጠርቷል። የአማኝ ፍቅር፣ የታይታ፣ ወይንም የከንፈር ወይንም ግብዝነት የሞላበት ሳይሆን "ከልብ" የሆነ እንዲሆን ይገባል። የቅድስናን ኑሮ አማኝ የሚለማመደው በግል ኑሮ ብቻ ሳይሆን ከወገኖች ጋር በሚኖረው ሕብረትም ጭምር ነውና። ይህ ክፍል በተጨማሪ ከማይጠፋ ዘር መወለዱን አውቆ እንደ ሣር በሚጠወልግ በዚህ ምድራዊ ነገር መያዝ የለበትም ይላል።

### *መደምደሚያ*

ከሁሉ በፊት ክርስቲያን መሻቱ ወደ ፊት የሚጠብቀው ድነት ሊሆን ይገባል፤ በዚህም ምድር በእንግድነት እንዳለ ማወቅ አለበት። ሌላው ራሱን ከኃጢአት

መለየት መቻል አለበት። መቀደስ ማለት መለየት ማለት ነው (1ጴጥሮስ 1፡15-16)። ነገራችንን ሁሉ ለጌታ ብንሰጥ ጌታ የነገሩ ባለቤት እንደሆነ አውቀን ስለ ጌታ በጽድቅ መንገድ መከራ መቀበል በሕይወት ያሳድገናል። እኛ በደም የተዋጀን የጌታ ልጆች ነን።በማንኛውም ጊዜ ከዚህ ጠፊ ከሆነው ዓለም ራሳችንን ማዳን አለብን። ድነት ታላቅ ሥጦታ ነው! ሰው በራሱ ጥሮ እና ግሮ ሊያገኘነው የማይችል ንጹህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ሆኖም ግን ይህ ስጦታ ያለ ኃላፊነት አልመጣም። ይህንን ድነት የተቀበለ ሁሉ ድነቱን የሚመጥነውን የቅድስና ኑሮ እንዲኖር አማኝ ሁሉ ተጠርቷል። ስለዚህም እኛም በድነታችን ተደስተን፣ በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ደግሞ ድነታችንን የሚመጥን የቅድስና ኑሮ እንድንኖር ይሁን!

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. 1ጴጥሮስ 1፡13-14 ካለፈው ጥናት ጋር ምን ግንኙነት አለው? በተለይም ቁ.13 ላይ "ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ..." የሚለው መልዕክት ምንን ያገናኛል ወይም ያመለክታል?
2. ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ አማኝ መሻቱ ወደፊት መሆን ያለበት ምንድ ነው ?
3. 1ጴጥሮስ 1፡13 "አስቀድማችሁ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ" ሲል ምን ማለቱ ነው? ማንን ያመለክታል?
4. 1ጴጥሮስ 1፡15-16 ዘሌ 19፡2 እና 24 መሰረት አማኝ የተጠራው ለምንድ ነው?
5. መቀደስ ማለት ምን ማለት ነው? ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ ጌታ ቃል ያልተቀደሰ ሰው ቢገጥመን ምላሻችን ምንድ ነው?
6. 1ጴጥሮስ 1፡17-19 በማንበብ ዋናውን ነገር ተወያዩ።
7. 1ጴጥሮስ 1፡21-25 በማንበብ የተረዳችሁትን ነገር ተነጋገሩ። በተለይም ቁ.22፣23 እና 24 ከምዕራፉ ሀሳብ ጋር ምን ይገናኛል?
8. ዛሬ ምን ተረዳችሁ፣አጠገባችሁ ላለው ሰው ንገሩት። ምን የጸሎት ርዕስ አገኛችሁ?

## ጥናት አራት

## የንባብ ክፍል 1ጴጥሮስ 2:1-10 የአማኞች መሠረትና የተሰጣቸው ኃላፊነት

**ዓላማ፡-** በተናቀ ነገር ግን የማዕዘን ዐለት በሆነው በክርስቶስ ሞትና ትንሳዔ የሚያምን ክርስቲያን በእምነቱ እንዳያፍር በመንገር የክህነት ኃላፊነት እንዳለበት ማሳወቅ

**መግቢያ፡-** ከማይጠፋ ዘር የተፈጠርን ነን። በዚህ በማይጠፋ ዘር ታዲያ እንዴት ልንቀሳቀስ እንችላለን የሚል ጥያቄ ሲነሳ ደግሞ መልሱን በዚህ ጥናት እናገኛለን። በተጨማሪም ይህ ጥናት አማኞች ስላገኙት ክብርና መለኮታዊ አደራም ይናገራል፤ ያብራራልም (1ጴጥ 2፡8-10) ።

## 1ጴጥሮስ 2:1-10

## ለዚህ ጥናት 1ጴጥሮስ ምዕራፍ አንድ የመጨረሻዎቹ ሶስት ቁጥሮች እንነሳለን

“23 ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ። 24 ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና፤ ሣሩ ይጠወልጋል አበባውም ይረግፋል፤ 25 የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል። በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው (1ጴጥ 1፡23-25)።”

1. ***ወደ ማይጠፋ ዘር መቅረብ*** (1ጴጥ 2፡1-3) **፡-** ስለዚህ ወደዚህ ወደ ማይጠፋ ዘላለማዊ ዘር እንዴት እንቅረብ?

በነዚህ ቁጥሮች **“እንግዲህ”** ብሎ የሚጀምረው ቃል ካለፈው ምዕራፍ ሀሳብ ጋር ይያያዛል ማለትም “24ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና፤ ሣሩ ይጠወልጋል አበባውም ይረግፋል፤25የጌታ ቃል ግን ለዘላለም **ይኖራል። በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው።**” እንደዚህ ከሆነ በ1ጴጥ 2፡1-2 ላይ ወደ ማይጠፋ ዘር አምስት ነገሮችን በማስወገድ እንቅረብ ይላል፡- እነርሱም **ሀ.**

ከፋትን **ለ.** ተንኰልን **ሐ.** ግብዝነትን **መ.** ቅንዓትንና **ሠ.** ሐሜት ናቸው። ለማደግ ደግሞ ጤነኛ ህጻን የእናቱንም ጡት ይሁን ሌላም ወተት እንደሚመኝና እንደሚያስፈልገው የጌታ ቃል ለአማኞች እንደ መንፈሳዊ ምግብ ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ መንፈሳዊ ረሃብ ሁል ጊዜ ልንራብ ያስፈልጋል። ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ከ1ቆሮ 3፡1 እና ዕብ 5፡12 ጋር ተቃራኒ ነው። በዚያ ክፍል ለላደጋችሁም ገና ህጻን ሰለሆናችሁ ጠንካራ ምግብ መመገብ አትችሉም ይላል። ማለትም ጠንካራ መንፈሳዊ ምግብ መመገብ የሚችሉበት የክርስትና እድሜ ላይ ሆነው ግን አይመገቡም ነበር። መዝ 42፡1-2 "1 ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥ አቤቱ፥ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች። 2 ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች መቼ እደርሳለሁ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ?"። ለእኛ ወደ እርሱ መቅረብ ይሻለናል። የሞተውን የሥጋን ሥራ ካስወገድን እንደ ተራበ ህጻን የቃሉን ወተት በመመኘትና በመጠጣት መንፈሳዊ እድገት መተካት አለብን። ወተቱ የጌታን ቸርነት የሚናገር ነው። የጴጥሮስ መልዕክት ተቀባዮች በርግጥ የጌታን ቃል ደስታ ተለማምደዋል። አሁንም ቀጥሉ ይላቸዋል። ደግሞም ያደገ ዛፍ ያፈራልና መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራትም እጅግ አስፈላጊ ነው።

## 2. የማዕዘን ድንጋይና ሕያዋን ድንጋዮች (1ጴጥ 2፡4-6) ፡-

አማኞችን ወደ እርሱ ወደ ክርስቶስ እየቀረባችሁ መንፈሳዊ ቤት በመሆን ተሰሩ በማለት ትልቅ ትምህርት ያስተምራል። እንዴት? ለሚለው ጥያቄ ወደ ማእዘኑ ድንጋይ ወይም ወደ ህያው ድንጋይ በመቅረብ ወይም በመገጣጠም ይሆናል። የማእዘኑ ድንጋይ ባህርይ (ማንነት) በ1ጴጥ2፡4 ተጠቅሷል፤ እንደ ሚከተለውም ይላል **ሀ. "በሰውም ወደ ተጣለ"** ይህ መልዕክት አይሁዶችም ይሁን ሌሎች ክርስቶስን መግፋታቸውን የሚያሳይ ሀሳብ ነው። **ለ. "በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደ ተመረጠ"** ነገር ግን ሰው ቢጥልም እግዚአብሔር ከዘፍጥረት ጀምሮ በቃል ኪዳኑ ክርስቶስን መምረጡን የሚያሳይ መልእክት ነው፤ ሐ. **"ክቡር ወደ ሆነው ወደ ሕያው ድንጋይ"፥** ጴጥሮስ ሰው የጣለው ይሁን እንጂ ድንጋዩ ክቡርና ህያው ነው ብሎ ያረጋግጣል። ስለ ወርቅ ወይም አልማዝ ማወቅ የሚገባው ልጅ እውቀቱን በራሱ ምክንያቶች አልፈልግም ካለ ወርቅ ወይም አልማዝ ክቡር መሆኑን አያውቅም። ሊጥለው ወይም ሊጫወትበት ይችላል። ልጅ የአባቱን ትልቅነትና ማንነት ካላወቀ ለራሱም ዋጋ ያሳንሳል። ወደ ተጣመመም መንገድ ሊሄድ ይችላል። እምነትና እውቀት እጅግ ጠቃሚ ነገሮች ናቸው። ይህ ደግሞ የሚገኘው ወደ እርሱ

ወደ ክርስቶስ በመንፈሳዊ ህንች አማካይነት በመቅረብ ነው። ቁ.5 እንደሚነግረን የክህነትን ሥራ እየሰራን ማለትም በማስታረቅ ሥራ እያገለገልንና ምስጋና እያቀረብን በቤቱ ካሉት ድንጋዮች እንደ አንዱ ነን ይላል።

ለዚህም ጴጥሮስ ከብሉይ ኪዳን ኢሳ 28፡16ን ይጠቅሳል። ይህ ክፍል ሰለ ድንጋዩ ማንነት ማጠናከሪያ ሶስት ነገሮችን ያስቀምጣል ሀ) **የተመረጠ** ለ) **የከበረ ሐ) የማዕዘን ራስ ድንጋይ** እንደሆነ ይናገራል (1ጴጥ 2፡6)። ስለዚህ ይህ እንደ ማይፈርስ ጠንካራ የማዕዘን ድንጋይ የተነገረው የማያሳፍር ስለሆነ አማኝ ሁሉ በእርሱ በማመንና እንደ ቤት በመሰራት ይኖራል። ሐዋሪያው ጴጥሮስ በሐዋ 4፡11 ይህንኑ ሀሳብ ተናግሯል። ክርስቶስ እውነተኛ ሐዋሪያ፣ነቢይ፣ንጉስ፣ካህን ነው። ክርስቶስ የቤቱን ማዕዘን የያዘ ጠንካራ ድንጋይ ነው። አማኞች ወደዚህ የማእዘን ድንጋይ ከመጡ በኋላ ዋና መሠረታቸው ስለሆነ በመከራ ውስጥ ቢያልፉም እንኳን ምንም አይሆኑም፤አይናወጡም። ጠንካራ መሰረት ያለው ቤት ነው።

## 3. ከተናቀ ከሚመስል ከላቀ የማዕዘን ድንጋይ የሚገኝ የላቀ ክብር ማንነት (1 ጴጥሮስ 2፡7-8)

ባለሙያ በትኩረት ካላየ በስተቀር ቤት ሲሰራ አንዳንድ ድንጋዮች የማይጠቅሙ ይመስላሉ ነገር ግን እጅግ ጠንካራና የቤት ማዕዘንም ሊሆኑ ይችላሉ። **“7ሀ.እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ለምታምኑት ነው፤...”** ሐዋርያ ጴጥሮስ የማዕዘን ድንጋይ የሚል ሀረግ ይደጋግማል። ከላይ እንደተጠቀሰው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አራት በሰበከውም ስብከት ስለዚህ ድንጋይ ተናግሯል “እናንተ በሰቀላችሁት እግዚአብሔርም ከሙታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደኅና ሆኖ በፊታችሁ እንደ ቆመ፥ ለእናንተ ለሁላችሁ ለእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ የታወቀ **ይሁን።እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት፥ የማዕዘን ራስ የሆነው ይህ ድንጋይ ነው።መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።” አይሁዶች ጌታን ንቀውታል።** “22ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፥ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ፥ 23ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፥ ለዓይናችንም ድንቅ ናት። 24እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት ሐሤትን እናድርግ፥ በእርስዋም ደስ ይበለን” (መዝ 118፡22-24)።

በመቀጠልም ይህ የማዕዘን ድንጋይ የከበረ ብቻ ሳይሆን በእርሱ የሚያምንም የዚህ ክብር ተካፋይ ነው ብሎ ያረጋግጣል። የማዕዘን ድንጋይ ከቤቱ ከላይ ማዕዘን ብቻ ሳይሆን የሚቀመጠው በቤቱ መነሻ መሠረት ላይም እንደሆነም ብዙዎች ያምናሉ።ይህ ለቤቱም ጥንካሬ ወሳኝነት አለው። በዚህም የማዕዘን ድንጋይ ላይ ብዙ ድንጋዮች ይገነቡና ቤት ይሆናሉ። ወደ ድነት ስናመጣ ጌታን ያመኑ አይሁድና አህዛብም በዚህ መሠርት ላይ ተመስርተዋል።የዚህ መንፈሳዊ ቤት አንድ አካል መሆን ትልቅ ክብር ነው።

በተመሳሳይ ደግሞ በዚህ የማዕዘን ድንጋይ ህያዋን ሆነው ያልተቀመጡ የቤቱ አካል አይደሉም **“7ለ. ለማያምኑ ግን አናጢዎች የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ የዕንቅፋትም ድንጋይ የማሰናከያም ዓለት ሆነ፤ 8 የማያምኑ ስለ ሆኑ በቃሉ ይሰናከሉበታልና፤ ለዚህ ደግሞ የተመደቡ ናቸው”።** ወንጌል (ግብዣ) ለሁሉም እኩል ተሰጥቶአቸዋል ነገር ግን ይህንን ግብዣ የተጠቀሙ ሰዎች ሁሉ ለደህንነት የተመደቡ ሲሆኑ ግብዣውን አልመጣም ወይም አንመጣም ያሉ ደግሞ በራሳቸው ፈቃድና እውቀት ለጥፋት ከተመደቡ ወገን ይሆናሉ (ማቴ 14፡16-23)።

## 4. የአማኞች ማንነትና ኃላፊነት (1ጴጥ 2፡9-10)

ከላይ ቁ.8ን ባጠናነው መሰረት ከጨረሰ በኋላ ቁ. 9ኝን ሲጀምር “9 እናንተ ግን...” በማለት ከቁ.8 ሀሳብ ጋር እያነጻጸረ ይቀጥላል። ቁጥር 9 መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከታወቁ ጥቅሶች አንዱና ከዘጸ 19፡5-6 ጋር የሚገናኝ ክፍል ነው። ዘጻዓት እንደዚህ ይላል “5 አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ 6 እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ (ዘጸ 19፡5-6)።” ይህ ክፍል (1ጴጥ 2፡9-10) አማኞች መከራ ውስጥ ቢሆኑም ያላቸውን ክብርና አገልግሎትን ያስረዳል። ጨለማ ውስጥ እንደነበሩና አሁን ደግሞ እንዴት በብርሃን እንዳሉም ይናገራል። የሚያሳድዱአቸውም ሰዎች በጨለማ ውስጥ ናቸው። የአማኞችም ማንነታቸው እንደሚከተለው ተብራርቷል **1. የተመረጠ ትውልድ፥** 2. **የንጉሥ** **ካህናት፥** 3. **ቅዱስ ሕዝብ፥** 4. **ለርስቱ የተለየ ወገን** መሆኑን ያስተምራል ። ስለዚህ አማኝ የክርስቶስን በጎነት በማወጅ እንደ ጌታ ወገን ምህረት እንዳገኘና እንደ ካህን ህዝቡን ከክርስቶስ ጋር የማስታረቅ ትልቅ እድልና ኃላፊነት አለበት። ይህ ክፍል ከምንም በላይ የቃል ኪዳን ህዝብ መሆናችንንም ያስረግጣል።

## መደምደሚያ

በተፈጥሮ ህግ ጤነኛ ሆኖ የተወለደ ህጻን ያድጋል። ይህ ደግሞ እውነተኛ የተፍጥሮ የህይወት ሂደት ነው። እንደዚሁም በመንፈስም ዳግም የተወለደ እወነተኛ የክርስትናን እውቀት ያገኘ አማኝ በመንፈስ ማደግ አለበት። ይህን ለማብራራትም ወዴት ነው የተጠራነው? የጠሪውስ ማንነት ምን ይመስላል? ብለን ስንጠይቅ በአጭሩ መልሱም የተናቀ የነበረ ግን የማዕዘን ዐለት ነው። ተጠሪዎችስ ያገኙት ክብር ምን ዓይነት ነው? ለተጠሩትስ የተሰጣቸው መለኮታዊ የቤት ሥራ ምንድ ነው? ለዚህም መልሱ በጌታ ህያው ቤት ሆኖ መሰራትና የክህነትን ሥራ መሥራት ነው (1ጴጥ 2፡9)።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. 1 ጴጥሮስ 2፡1-3 ከምዕራፍ 1፡22-23 ጋር ይገናኛል ወይስ አይገናኝም? እንዴት?
2. የ1 ጴጥሮስ 2፡1-3 ዘይቤአዊ የወተት ንግግር ከ1ቆሮ 3፡1 እና ዕብ 5፡12 ጋር እንዴት ተቃራኒ ሊሆን ቻለ?
3. 1ጴጥ 2፡4-6 የማዕዘን ድንጋይና ሕያዋን ድንጋዮች ተብሎ የተቀመጠው ምንድ ነው? ለማን ነው? " ግንበኞች የናቁት ድንጋይ ማለትስ ምንድ ነው?" ማን ነው የናቀው?
4. 1 ጴጥሮስ 2፡7-8 "ከተናቀ ከሚመስል ከላቀ የማዕዘን ድንጋይ የሚገኝ የላቀ ክብር ማንነት" በሚል ነጥብ በዚህ ጥናት ከተብራራው ያገኛችሁትን እውቀት ተወያዩ።
5. ከ1ጴጥ 2፡9-10 የአማኞችን ማንነትና ኃላፊነት በግልጽ ተወያዩ፤ከፍሉን ከዘጸ 19፡5-6 ጋር እንዴት ማገናኘት ይቻላል?
6. 1ጴጥ 2፡9-10 በህይወታችን ምን ትርጉም አለው? በህይወታችን ይህ ፍሬ እንዲያፈራ ጸሎታችን ይሁን።
7. ከዛሬ ትምህርት ምን ተማራችሁ? ለቡድኑ አካፍሉ።

# ጥናት አምስት

## የንባብ ክፍል 1 ጴጥሮስ 2:13-17

## *ለጌታ ብላችሁ <u>በሚገባ ነገር</u> ሁሉ ለሀገር መሪዎች ታዘዙ፡-ክርስቲያንንና ባለ ሥልጣናት*

**ዓላማ፡-** አማኝ እንደ ሰማያዊና ምድራዊ ዜጋ በምድር ላይ እንዴት መኖር አለበት? ለሚለው ጥያቄ እውቀት ማስጨበጥ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ነው።

**መግቢያ፡-** ክርስቲያን ለዚህ ምድራዊ መንግስት ህግ መገዛት አለበት ወይስ የለበትም? መገዛት ካለበትስ እስከ ምን ድረስ መሆን አለበት? ባይገዛ ለሚመጡ ችግሮች ማን ሊጠየቅ ይችላል? ታዲያ አንገዛም በማለታቸው እነ ዳንኤልና ጓደኞቹ ለችግር ለምን ተዳረጉ? ተሳስተዋል ማለት ነው? እንደዚሁም ሐዋርያትም? በዚህ መሰረት ለሚያስተዳድሩን ባለሥልጣናት ባንታዘዝ ምን ውጤት ይኖራል? እስከ ምን ድረስ እንታዘዝ? በተጨማሪም መታዘዝ ያለብንንና የሌለብንም መርሆችን (principles) በዚህ ጥናት እንመለከታለን። የጌታ ቃል በተለያዩ ቦታዎች አማኞች ለመንግስት ህግ መገዛት አለባቸው ብሎ ያዛል (ሮሜ 13፡1-6፣1ጢሞ 2፡1-2) ። ይህ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እናጠናለን።

### 1. 1ጴጥሮስ 2፡11-12 በእንግድነት ምድር በሌሎች መካከል ጌታን በሚያስከብር ኑሮ ኑሩ

በዚህ ክፍል በመከራ ውስጥ በጌታ የዳኑ ሰዎች ከሥጋዊ ምኞት ካልራቁ በስተቀር ኃጢአት ነፍሳቸውን ሊወጋ እንደሚችል ያስረግጣል። ስለዚህ ያንን አታድርግ ብሎ ያዛል። የሚርቁበትንም ምክንያት በጥሩ ምሳሌ ያስቀምጣል ማለትም <u>እንግዶችና መጻተኞች</u> ስለ ሆንን ማለት ነው። እንግዳ የሆነ ሰው እንደልቡ መሆን አይችልም። ምክንያቱም ቤቱ የእርሱ አይደለም። ይህ ምድር የክርስቲያን ዘላለማዊ ቤት አይደለም። ጴጥሮስ ተመሳሳይ ስም በ1ጴጥ 1፡1-2 ይናገራል "1-2 … በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት በጳንጦስና በገላትያ በቀጳዶቅያም በእስያም በቢታንያም **ለተበተኑ መጻተኞች፤** ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ" ይላል። እንደደዚሁም የዕብራዊያን ጸሐፊም እንደሚከተለው ተናግሯል "እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፥

የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና፤ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት፥ በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ" (ዕብ 11፡13)። ዳዊትም በብሉይ ኪዳን በጸሎቱ ይህንን ተመሳሳይ ሀሳብ ይናገራል "15 አባቶቻችንም ሁሉ እንደነበሩ እኛ በፊትህ ስደተኞችና መጻተኞች ነን ዘመናችንም በምድር ላይ እንደ ጥላ ናት፥ አትጸናም" (1ዜና 29፡15) ይላል። ስለዚህ እንደ እንግዶች ነፍስን ከሚወጋ ኃጢአት ወይም ሥጋዊ ምኞት መራቅ ራሳችንን ከጦርነት መጠበቅ ነው። ሥጋዊ ምኞት ደግሞ የዚህን ምድር ቤት ሀብት ለማፍራት ከመጠን በላይ በማሳብ የሰማይን ቤት እስከ መርሳት መድረስ ነው። መራቅ ማለት ደግሞ ከኃጢአተኛ ህዝብ መካካል ሸሽቶ መሄድ አይደለም ነገር ግን "በአሕዛብ መካከል" ኑሮአችን መልካም እንዲሆን ቁ.2 ላይ እንደሚጠይቀን በተቀደሰ ህይወት በመካከላቸው መኖር ነው። ዓላማውንም ሲገልጥ እንዲህ ይላል "ስለሚመለከቱት ስለ መልካም ሥራችሁ፥ ክፉ እንደምታደርጉ በዚያ እናንተን በሚያሙበት ነገር፥ በሚጎበኝበት ቀን እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ…" ይላል። በዚህ ክፍል "በሚጎበኝበት ቀን" ማለት **ጌታ ነፍሳቸውን ሊፈልግ ወደ እነርሱ ሲመጣ ለማለት እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ወይንም ህይወታችንን ሲያይ የሚለውንም ሀሳብ ያጠቃልላል።**

## 2. 1ጴጥሮስ 2፡13-14 ነገስታትን ማን ሾማቸው? ለምንስ እንገዛለን? ከመከራ ጋር እንዴት ይገናኛል?

በጴጥሮስ ጊዜ ከአይሁድ የተወሰኑ ክፍሎች ሌላ ንጉስ የማይፈልጉ ስለዚህም ቀረጥና ግብርንም ለመክፈል የሚያምጹ ነበሩ። በዓለም ዙሪያም ተበትነው ነበር። አዋጃቸው የእግዚአብሔርን ገንዘብ ብቻ እንሰጣለን ነው! ጴጥሮስ ግን ይህ አያስፈልግም ለሰው ሁሉ ሥርዓት በመገዛት የተቃዋሚዎችን ተቃውሞ እናጠፋለን ይላል። 13 "ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ፤ ለንጉሥም ቢሆን፥ ከሁሉ በላይ ነውና፤ 14 ለመኳንንትም ቢሆን፥ ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣት በጎም የሚያደርጉትን ለማመስገን **ከእርሱ ተልከዋልና ተገዙ (1ጴጥ 2፡13-14)።"** እግዚአብሔር በምድር ላይ ካስቀመጣቸው ተቋማት አንዱ መንግስት ነው ማለትም ጋብቻንና ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ ማለት ነው። ይህንን ያደረገው ደግሞ የሰው ልጅ ለኃጢአትና ለሰይጣን ተንኮል ራሱን በማስገዛት የሰውን ዘር ለማፍረስ መጠቀሚያ መሳሪያ

ስለሚሆን እንዳይጣፉ ለመከልከል ነው። ክርስቲያን ለጽድቅና እወነተኛ ለሆኑ ነገሮች መገዛትና ጥሩ ዜጋ የመሆን ኃላፊነት አለበት። ጌታ ኢየሱስ ትክክለኛ በሆነ መልኩ ወይም **በሚገባ ነገር** ለሀገር ህግ ይገዛ ነበር "17እንግዲህ ምን ይመስልሃል? ንገረን ለቄሣር ግብር መስጠት ተፈቅዶአልን ወይስ አልተፈቀደም? አሉት።18ኢየሱስም ክፋታቸውን አውቆ። እናንተ ግብዞች፥ ስለ ምን ትፈትኑኛላችሁ?19 የግብሩን ብር አሳዩኝ አለ። እነርሱም ዲናር አመጡለት።20እርሱም፦ ይህች መልክ ጽሕፈቲቱስ የማን ናት? አላቸው።21የቄሣር ነው አሉት። በዚያን ጊዜ። እንኪያስ **የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ** አላቸው።22ይህንም ሰምተው ተደነቁ፥ ትተውትም ሄዱ (ማቴ 22፥17-22) ።"

በብሉይ ኪዳን ዳንኤል ንጉስን እግዚአብሔር እንደሚሾም ይናገራል "20 ዳንኤልም ተናገረ እንዲህም አለ፦ ጥበብና ኃይል ለእርሱ ነውና የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ 21 ጊዜያትንና ዘመናትን ይለውጣል ነገሥታትን ያፈልሳል፥ ነገሥታትንም ያስነሣል ጥበብን ለጠቢባን እውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል።22የጠለቀውንና የተሠወረውን ይገልጣል በጨለማ ያለውን ያውቃል፥ ብርሃንም ከእርሱ ጋር ነው። ...37አንተ፥ ንጉሥ ሆይ፥ የሰማይ አምላክ መንግሥትንና ኃይልን፥ ብርታትንና ክብርን የሰጠህ የነገሥታት ንጉሥ አንተ ነህ።38በሚቀመጡበትም ስፍራ ሁሉ የሰው ልጆችንና የምድር አራዊትን የሰማይ ወፎችንም በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል፥ ለሁሉም ገዥ አድርጎሃል አንተ የወርቁ ራስ ነህ (ዳን 2፥20-22፤37-38)።"በተጨማሪም ብሉይ ኪዳን እንደሚነግረን ፈቃዳቸውን ካስገዙ ከጥሩ ነገሥታት ጋር ጌታ አብሮ ይቆም ነበር።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ለምን እንደምንገዛ ዋናውን ምክንያት ሲናገር 1. "ስለጌታ ብላችሁ" 2. "ከእግዚአብሔር ተልከዋልና" ብሎ ይላል። የተላኩብትም ምክንያት "ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣት በጎም የሚያደርጉትን ለማመስገን" ነው ብሎ ያስረግጣል። ዓለም እንደዚ ባይሆን ኖሮ ሰው መኖር አይችልም፤ ሥርዓትም አይኖርም።

ቁ. 15 እንደሚነግረን የጌታን ፈቃድ የምናደርገው የሚቃወሙን ሰዎች በእኛ ላይ እውነትን የያዘ ክስ ሲያጡ ነው። በለመገዛት አማኝ በራሱ ላይ መከራ ማምጣት አለመብሰል ነው። ለጌታ ቃል በመገዛት የጌታ ስም በዚህ ይከበራል።

### 3. **1ጴጥሮስ 2፡17-18 ታዲያ በጌታ የዳነ ሰው ነጻነቱ ምንድ ነው?**

“16 **አርነት** ወጥታችሁ እንደ እግዚአብሔር ባሪያዎች ሁኑ እንጂ **ያ አርነት** ለክፋት መሸፈኛ እንዲሆን አታድርጉ። **17 ሁሉን አክብሩ፥** ወንድሞችን ውደዱ፥ እግዚአብሔርን ፍሩ፥ **ንጉሥን አክብሩ።”** አንዳንዶች በክርስቶስ ሲድኑ ሁሉም ነገር ማለትም የአገዛዝ ሥርዓቶች የማይገዛቸው ይመስላቸዋል። እንደዚህ ዓይነት ነጻነት “ልቅ ነጻነት” ይባላል። ይህም የስህተት ትምህርት “አንትኖምኒዝም-Antinominism” ይባላል። ስለዚህ ሐዋርያው ጴጥሮስ ነጻነታችሁን በሚገባ ቦታ ተጠቀሙ ብሎ ያስተምራል። ነጻነታችን ወንድሞችን መውደድን፣ለሌሎች መገዛትን፣ሌሎችን ማክበርንና ጌታን መፍራትን ያጠቃልላል።

**ሐዋርያው ጳውሎስም በሚከተሉት ክፍሎች ይህን ሀሳብ ይደግፋል። ሮሜ 13፡1- 5**

“1ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። 2ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ። 3 ገዥዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፤ 4ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። 5ስለዚህ ስለ ቍጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስለ ሕሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው።” በዓለም ያሉት ሁሉም አማኞች ለሀገራቸው አስተዳደር አንገዛም ቢሉ ዓለም ምን ልትሆን እንደምትችል ማሰብ አይከብድም።

**ለሀገር መሪዎች መጸለይ እንዳለብን የጌታ ቃል ያስተምረናል።** 1ጢሞ 2፡ 1-2 “እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።” እንደ ክርስቲያን ኃጢአት ባልሆኑ ነገሮች ለሀገር ህግ መታዘዝና ለገዥዎችም መጸለይ አለብን። መጸለይም ያለብን ሰይጣን እንዳይጠቀማቸውና ጌታም በሉዓላዊነቱ እንዲመራቸው ነው።

## መደምደሚያ

አማኞች ለገዥዎች እንደሚገባ መገዛት አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚል ጥያቄ የብዙ ክርስቲያኖች ጥያቄ ነው። ነገር ግን የጌታ ቃል ለሁሉም መልስ አለው። አማኝ ጥሩ ሥነ ምግባር ያለው ሆኖ በዚህ እንግድነት ምድር መኖር አለበት። ይህም ደግሞ ለሌሎች ምስክር ለመሆንም ጭምር ነው። አማኝ ለጽድቅና ለእውነት ለማገንም የበላይ አለቃና ሀገር ሥርዓት መገዛት አለበት። ክርስቲያን ድምጽ አልባ መሆን የለበትም። ለሀገርም የመጸለይ ኃላፊነት አለበት።

## የመወያያ ጥያቄዎች (ለሁለት ቀን ጥናት ማድረግ ትችላላችሁ)

1. 1ጴጥሮስ 2፡11-12 ላይ የተጠቀሰው ሥጋዊ ምኞት ምንድ ነው? ወዴት ነው ራቁ ብሎ የሚያዛቸው?
2. ከሥጋዊ ምኞት ራቁ የሚላቸው ለምንድ ነው? ከኃጢአተኞች መካከል መውጣት አለብን?ካልሆነስ?
3. በዚህ ክፍል መስረተት እንግዳና መጻተኛ ማለት ምን ማለት ነው? ሌሎች ተመሳሳይ ጥቅሶች አሉ? ምን ያስተምረናል?
4. ከ1ጴጥሮስ 2፡13-14 ምን ተረዳችሁ?
5. አማኝ የሁለት ዓለም ዜጋ ነው (ሰማያዊና ምድራዊ) ለሁለቱም ጥሩ ሥነ ምግባር እንዲኖር ታዟል። ሁለቱንም እንዴት እንደሚመራ ተወያዩ። ሳይጋጭብን ለጌታ ክብር መኖር አለብን።

**6.** ጌታ ለነገስታት ህግ መታዘዝን እንዴት ነበር ያስተማረው (ማቴ 17፡25-27፤22፡17-22)?

**7.** ዳን 2፡20-22፤37-38 በማንበብ ከዚህ ጥናት ጋር ምን ግንኙነት እንዳለው ተወያዩ?

<u>ከዚህ በኋላ ያለውን ለሚቀጥለው ቀን ማስተላለፍ ትችላላችሁ</u>

8. በሮሜ 13፡1- 5 የሐዋርያው ጳውሎስ እምነት ስለ ነገስታት ያለው ትምህርት ከሐዋርያ ጴጥሮስ ጋር ምን አንድነት አለው?

9. 1ጢሞ 2፡ 1-2 "እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።" ይህ ጥቅስ ምን ያስተምረናል? ከዚህ ጥናት ጋር ይገናኛል?

10. ለነገስትታ ህግ መገዛት ያለብንና የሌለብን መቼ ነው።

11. ሐዋ ሥራ 4፡14-20 ጴጥሮስና ዮሐንስ እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ ነገር እንዳልሆነ ይናገራል። ይህን ለገዥዎች ከመገዛት ጋር እንዴት እናስማማለን?

12. ከዚህ ጥናት የተረዳሁትን ላካፍላችሁ። ዛሬ ለነገሥታት እንጸልይ።

# ጥናት ስድስት

## የንባብ ክፍል 1 ጴጥሮስ 2:18-25

## በመከራ ውስጥ ለመታዘዝ መከራ ከተቀበለው ከመሲሁ ህይወት እንማር

**ዓላማ፡-** ባሮች በጌታ ነጻ ከወጡ በኋላ ከጌቶቻቸው ጋር እንዴት መኖር እንዳለባቸው ማስተማርና በጌታ ነጻ የወጡ ሁሉም ክርስቲያኖች በመከራ ውስጥ ለመታዘዝ መከራ ከተቀበለው ከመሲሁ (ከክርስቶስ) ህይወት መማርን ማሳወቅ።

**መግቢያ፡-** ብዙ ጊዜ በጌታ ነጻ የወጣን አማኞች ግራ የሚገባን ነገር ቢኖር "ክርስቲያን ከሆንኩ በኋላ ለአለቆቼ እንዴት ልታዘዝ?" ይሆናል። እንደ አገራችን ከሆነም "የሰው ቤት ሰራተኛ ሆኜ ስቀጠር በምን መልኩ መገዛት አለብኝ?" የሚል ግራ የሚያጋባ ነገር ይኖራል። ይህ ግንኙነት በአሁኑ ዘመን ማንንም አማኝና የበላይ ኃላፊውን ሊመለከት ይችላል። ለነዚህ ጥያቄዎች በዚህ መልዕክት መልስ እናገኛለን። ባርያ በመሆንም ይሁን ባለመሆን በጽድቅ መከራ ስንቀበል ፍጹም ምሳሌያችን መሆን ያለበት ክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑን ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልዕክቱ ይናገራል። ስለ እኛ ክርስቶስ ሁሉን አድርጓል ብሎም ያስረግጣል። እነዚህንና ሌሎችንም በዚህ ጥናት እናያለን።

## ሀ. 1ጴጥሮስ 2፡17-20 የባሮች ኑሮና ክርስትና የሰጣቸው ነጻነት

በባለፈው ጥናት 2፡17 ላይ ለሁሉም ማለትም ለጌቶችም ሆነ ለባሪያዎች **"1) ሁሉን አክብሩ፥ 2)ወንድሞችን ውደዱ፥ 3) እግዚአብሔርን ፍሩ፥ 4)ንጉሥን አክብሩ"** በማለት አጠቃላይ ትዕዛዝ በመስጠት ጨርሷል። አሁን ደግሞ **ሎሌዎችን ወይንም ሰራተኞችን** ያስተምራቸዋል። ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው አንድ ሰው በክርስቶስ ነጻ ሲወጣ በሥልጣን ተዋረድ የነበረበትን ቦታ ለቆ እንዲያምጽ የጌታ ቃል አያዝም። ይልቁንም መንፈሳዊ የፍቅር ህግ በህይወቱ እንዲተገብር ያዛል። በዚህም ምክንያት ያላመኑ ሰዎች የጌታን ክብር ያያሉ። በወቅቱ ክርስቲያን በሆኑ ሰዎች ችግር የነበረው የክርስትናን ሙሉ ዕውቀት አለማግኘታቸው ነበር። በጌታ ነጻ ነህ ሲባል ለባልና ለአለቆች መገዛትና መታዘዝ ሁሉ ያቆመ ይመስላቸው ነበር። ነገር ግን ስህተት የሌለበት ክርስትና ግን ሰማይና ምድር ገና ሲፈጠር የአስተዳደር ተዋረድ እንዳለ

ማወቅ ነው። የሥላሴም ምሳሌ ጥሩ ማብራሪያ ነው። በሥራ መለያየት በሥልጣንን ዝቅተኛነትንና ከፍተኛነትን አያመለክትም። የሥራ ክፍፍል ብቻ ነው።

“ሎሌዎች ሆይ፥ ለበጎዎችና ለገሮች ጌቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለጠማሞች ደግሞ በፍርሃት ሁሉ ተገዙ **19 በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገሥ ምስጋና ይገባዋልና** (1ጴጥ 2፡18-19)።” እንዴት ለጠማሞች እገዛለሁ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል? ይህ ቃል ክርስቶስን ከማሳወቅ ጋር የተገናኘ መልዕክት ነው። ቁ.19 እንደሚነገረን ለምንቀበለው መከራ ሁሉ ጌታ ዋጋ ይመልሳል። ስለ ጌታ በግፍ መከራ መቀበልም ሊኖር እንደሚችል ያስተምራል። የሚከተሉት ጥቅሶች እጅግ ጠቃሚ መርህ ናቸው **“ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ”** (1ጴጥሮስ 2፡13)፣ “ **ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ” (ኤፌ 5፡21)። “ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፥ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት፥” (ቆላ 3፡23**)። **“5 ባሪያዎች ሆይ፥ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በልባችሁ ቅንነት በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ ታዘዙ፤6 የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ።7 ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በበጎ ፈቃድ ተገዙ፤8 ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው፥ እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና”** (ኤፌ 6፡5-8)። አማኝ መከራ ቢቀበል ጌታ ምስጋና የሚሰጠው ኃጢአት ሰርቶ ሳይሆን ለጽድቅ ብሎ ሲጋፈጥ ብቻ ነው። ስለዚህ ይህ ደግሞ ብዙ ትዕግስት የሚጠይቅ ነገር ነው (ቁ.20)።

## ለ. 1ጴጥሮስ 2፡21-23 በመከራ ውስጥ ለሚያልፉ ክርስቲያኖች የክርስቶስ ምሳሌ

“21 የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና።” እኛ የተጠራንበት አንዱም ዓላማ በኃጢአት በተበከለ በዚህ ዓለም ፍትህ ሲጓደል ስናይ በጸሎትና በትዕግስት እንድናልፍ ነው። ማንኛውም አማኝ ትልቅ ክብርና መብት በዚህ ምድር እንዳለው

ማሰብ ሊሆን የማይችል ነገር ነው። በተለያዩ ቦታዎች በተለይም በዓለማዊያን መካከል አማኝ በጎ ነገር ቢያደርግም መከራ ሊቀበል ይችላል። ክርስቶስ ሰዎችን እየፈወሰ፣ ህይወት እየሰጠ፣ ትክክለኛ የኑሮ ምግባርንም እያስተማረ፣ከሞትም እያስነሳ፣ ወዘተ … ነገር ግን በጌታ ላይ መከራው እየጨመረ ይሄድ ነበር። ይህን ሐዋሪያው ጴጥሮስ በዓይኑ አይቶታል።

ሐዋሪያ ጳውሎስም በ2ቆሮ 5፡16-18 እንደሚከተለው በማለት ስለ መከራ ያስተምራል “16ስለዚህም አንታክትም፥ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል። 17-18 የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው”። ስለዚህ ስለ ስሙ፣ስለ ወንጌል፣ስለ ጽድቅና ስለ እግዚአብሔር መንግስት መከራ ልንቀበል እንደምንችል መልዕክቱ ያስተምረናል። ነገር ግን ሁሉም ጊዜያዊ ነገር ነው።

ጌታ መከራ በሚቀበልበት ወቅት ከመከራው ለማምለጥ ብሎ ኃጢአት አላደረገም። በአፉም መጥፎ ነገሮችን አልተናረገም፤ደግሞም አምላክ ሆኖ አልዛተም። ይህ ሲባል ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ለአባቱ ራሱን አሳልፎ መስጠቱን አልተወም። ጌታ አባታችን ጻድቅ ፈራጅ ነው።

## ሐ. 1ጴጥ 2፡24 25 ክርስቶስ ሰለ እኛ ሁሉን ካደረገ እኛ ምን እናድርግ?

**“24 ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤”**

ለኃጢአት ሞተን፡- ሞት ከመለየት ጋር የተገናኘ ነገር ነው። ሰው ሲሞት ከሰው ይለያል። ከዚህ ዓለም ተለይቶ ወደ ሌላ ዓለም ይሄዳል። እንደዚሁ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞቱና ትንሳዔ ዓላማ አማኞች ለኃጢአት ሞተው ወይንም ከኃጢአት ተለይተው ለጽድቅ ሥራ እንዲኖሩ ነው። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ሁሉን ሰርቶላቸው በዔደን ገነት አስቀመጣቸው። ሲያስቀምጣቸው ግን ላዘዛቸው ትዕዛዝ እንዲኖሩ ነበር። እንደዚሁ ክርስቶስ ስለ እኛ ሁሉን አድርጎ ነገር ግን በጽድቅ

እንዲንኖር ኃላፊነት ሰጠን። ሰው ከመጀመሪያ ጀምሮ ማድረግ ለሚችላቸው ነገሮች ኃላፊነት ተሰጥቶታል። ክርስቶስ እንደ ሊቀ ካህን፣ነቢይ፣ንጉስ ሰው ሆኖ ሁሉን ፈጽሟል። በኃጢአት ቢፈተንም ለኃጢአት አልተሸነፈም። ሰው ሆኖ መጥቶ የሰውን ድካም አስወግዷል።

“2 ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? … 4 እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን። 7-8ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን፤9ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና (ሮሜ 6፡2፣4፣7-9) ።” መከራ ውስጥ ብናልፍም ህያው ሆነን መኖር እንደምንችል ማወቅ አለብን።

25 በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ። እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፥ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል። ወደ ነፍሳችን እረኛና ጠባቂ  መመለስ የቻልነው በክርስቶስ መገረፍ ምክንያት ነው። “እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና” የሚል ሀሳብ ነው። እረኛ የሌለው በግ ትክክለኛ ምግብ አለመመገቡ ብቻም ሳይሆን ለአውሬ የተጋለጠ ይሆናል። ስለዚህ በክርስቶስ እረኝነት ውስጥ ስንገባ መከራም ቢገጥመንም የነፍሳችን እረኛና ጠባቂ አለን።

### መደምደሚያ

ይህ መልዕክት ከምንም በላይ ለሁሉም በመከራ ውስጥ ለመታዘዝ መከራ ከተቀበለው ከመሲሁ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት መማር አለብን ነው። ባሮችም ይሁኑ ሌሎች በሰው ሥር የሚሰሩ ስለ ጌታ እንደሚሰሩ አስበው እንዲሰሩ ያሳስባል።  1ጴጥሮስ 2፡21-23 በመከራ ውስጥ ለሚያልፉ ክርስቲያኖች የክርስቶስ ምሳሌ ሁነኛ  ነገር ይላል። በምዕራፉ መጨረሻም 1ጴጥሮስ 2፡24-25 ክርስቶስ ሰለ እኛ ሁሉን ካደረገ እኛ  ለኃጥአት ሞተን ለጽድቅ እንኑር ይለናል።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. 1ጴጥሮስ 2፡18 “ሎሌዎች ሆይ፥ ለበጎዎችና ለገሮች ጌቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለጠማሞች ደግሞ በፍርሃት ሁሉ ተገዙ።” ይህን ቃል በህይወት መተርጎም ቃላል ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን? ከባድ ከሆነ እንዲቀለን የሚከተሉትን ጥቅሶች በማንበብ መሆን ያለበትን እንወያይ።
   “ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ” (1ጴጥሮስ 2፡13) ።
   “ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ” (ኤፌ 5፡21)።
   “ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፥ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት፥” (ቆላ 3፡23) ።
2. 1ጴጥሮስ 2፡18 ይህ ጥቅስ ከባለፈው ጥናት ጋር ይገናኛል?
3. 1ጴጥሮስ 2፡18-19 አማኝ መከራ እንዲቀበል የተጠየቀው በምን አይነት ጊዜ ነው? ለምን?
4. 1ጴጥሮስ 2፡21-23 በማንበብ ዋና መልዕክቱን ከአውዱ (ከክፍሉ) ጋር በማያያዝ ተወያዩ።
5. በመከራ ውስጥ የክርስቶስን ምሳሌ መከተል ምን ይጠቅማል?
6. ሮሜ 6፡1-13 በማንበብ የተረዳችሁትን ተወያዩ፤ከዚህ ጥናት ጋር ምን ይገናኛል?
7. በእኛ መካከል የሰራተኞችና የአሰሪዎች አስተዳደር አለ? እንዴት ነው የምናስተዳደራቸው ወይም የምንተዳደረው? ባይኖር እንኳን ይህ ጥቅስ ለምን ይጠቅማል ብላችሁ ታስባላችሁ?
8. ዛሬ ያገኘሁትን ትምህርት ላካፍላችሁ

## ጥናት ሰባት

የንባብ ክፍል፡ 1ጴጥሮስ 3:1-12

**“በቤተሰብ ውስጥ የመቀባበል ጸጋ”**

**ዓላማ፡-** ሰላምና በረከት የሞላበት ቤት፣ በጌታ ፍርሃት መቀባበል፣ መከባበርና መተሳሰብ የሚታይበት መሆኑን ማስገንዘብ።

**መግቢያ፡**

በ1 ጴጥ. 3:1-12 ስኬትና ሰላም የሞላው ቤት ለማየት ለባልና ሚስት ግሩም ምክሮችን እናገኛለን። ቤተሰብ የሚጸናው የክርስቶስን ፈለግ የሚከተሉ ባልና ሚስት ሲገኙበት ነው። ሁለቱም አማኝ ባይሆኑም አንዱ እንኳን የጌታውን ፈለግ ቢከተል ከውጣ ውረድ ባሻገር ጌታ የሚከብርበት ነገር እንደሚወጣው ጴጥሮስ ያስተምራል።

1ጴጥሮስ 3፡ 1 እና 7 ላይ የምናገኘው “እንዲሁም” የሚለው ቃል ዐውደ ምንባቡ ከ1ጴጥ 2:21-25 ካለው ሀሳብ ጋር የተያያዘ መሆኑን ያሳያል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመከራ ሲያልፍ ለአብ ፍቃድ ራሱን እንዳስገዛና እንደታዘዘ በቤት ውስጥም የዚህን ጌታ ፈለግ መከተል ለሚስቶችና ለባሎች የተሰጠ አደራ ነው።
ከዛሬው ጥናታችን በመልካም የምትመላለስ ሚስትና የአክባሪ ባል ህይወት ምን እንደሚመስል እንመለከታለን።

### በጌታ ፍርሃት የተመራ ንጹህ ኑሮዋ 1ጴጥ 3:1-6

በዚህ ክፍል ሚስቶች ልብ ሊሉት ስለሚገባ አብይ እውነት እንነጋገራለን።

**ሀ. ሚስቶች ሆይ ለባሎቻችሁ ተገዙ (3:1-4)**

**“ተገዙ”** ሲል ምን ማለት ነው? ይህን አሳብ 1ጴጥሮስ 3:1,5 እና ኤፌ 5:21ን አያይዘን መመልከቱ መልካም ነው። መገዛት ማለት የዝቅተኛነት ጉዳይ ሳይሆን ቤትን ለማጽናት ዝቅ የማለትን ሚናን ነው የሚያሳየን። በስብዕና ሚስቶች ከባሎቻቸው አንሰው፣ የበላይ ለሆኑ ባሎች ተዋርዶ የመኖር ጉዳይ አይደለም። በምንም መልኩ የዝቅተኛነት መግለጫ አይደለም።
መገዛት በጌታ ፍርሃት እግዚአብሔር ለመሠረተው ቤተሰብ ጤና የራስን መብት፤ ፍቃድ መስጠት ነው። ለመሆኑ ለምን ትገዛለች?

***ትዕዛዝ ስለሆነ፡-*** የተጻፈው በትዕዛዝ መልክ ነው። ተገዙ እንጂ ሌላ ምርጫን አላቀረበም።

***ለወንጌል የተከፈተ በር ስለሆነ***፡- በሚስቶች መገዛት ቤት ይጸናል። ትዳርን ከማጽናት ያለፈ ጉዳይም ነው። አማኝ ያልሆነ ባልን ለጌታ የመማርክ ኃይል አለው። ይህ ተግባር ድምፅ ሳያሰሙ ወንጌልን በህይወት የማሳያና የማስተማሪያ መንገድ ነው። ሚስት በተቀደሰ ባህርይዋ የጠፋችን ነፍስ ልትታደግ የምትችልበት ጸጋ ነው።

***የከበረ ዋጋ ያለውና የማይጠፋ ጌጥን የማሳያ ልዩ መንገድ ስለሆነ***፡- ከውጫዊ ውበት ይልቅ ማራኪ የሆነ ውበትን ማሳያ መንገድ ይህን ትዕዛዝ መለማመድ ነው።

- ***የውጭ የሆነ ጌጥ፡-*** አማኝ ሴት ውበቷን ለመጠበቅ የምታደርገውን ማጌጥ ትተው ሳይሆን፣ የውስጥ ማንነት ከውጫዊው የላቀ መሆኑን ነው የሚያሳስበው። ማራኪ ለመሆን ማጌጥ ብቸኛው መንገድ አይደለም። ጌጥ ብቻውን ቤትን አይሠራም።
- ***የልብ ሰው፡-*** የተሰወረ "የልብ ሰው" የሚገለጠው ሚስቶች በየዕለቱ በየዋህነትና በዝግተኛነት በሚኖሩት ኑሮ ነው። የዋህነት ደካማነት አይደለም፤ ራስን በመግዛት ዝቅ በማለት ነገሮችን የማድረግ ኃይል እንጂ። ለመገዛት ዝቅ ማለት ይህ መንፈሳዊነት ነው።

## ለ. የቀደሙ ቅዱሳን ሴቶችን በመገዛት መምሰል፡- (3:5-6)

- ምሳሌ፡- ሣራ ለአብርሃም በመታዘዝ ለሚስቶች ሁሉ ምሳሌ ነች። የቀደሙት ቅዱሳን ሴቶች ለባሎቻቸው ይዋቡ ነበር። ይህን እያደረጉ ደግሞ ጌታን ተስፋ በማድረግ ለባሎቻቸው ይገዙ ነበር። ለባሎች መገዛት አዲስ ነገር አይደለም፤ የቀደሙት ቅዱሳን ያደረጉት ነገር ነበር።
- ልጆችዋ መባል፡- ሚስቶች ያለፍርሃት በመታዘዝና መልካም በማድረግ ህይወት ከታወቁ ከሚገጥማቸው በረከቶች ውስጥ አንዱ የሳራ ልጆች መባል ነው። ይህ አባባል ስም የማግኘት ጉዳይ አይደለም። የቃል ኪዳን ህዝብ የመሆን መብት ነው።

## በጌታ ፍርሃት አደራውን የሚወጣ ባል 1ጴጥ. 3:7

በዚህ ምዕራፍ ሐዋሪያው ስለ ሚስቶች ብቻ አይደለም የሚናገረው ነገር ግን በቁጥር 7ና 8 ለባሎችም የሚሰጠው ምክር አለ። ባሎች የክርስቶስን ፈለግ በመከተል

የሚወጡት ታላቅ አደራ አለባቸው። ከሚስቶቻቸው ጋር አብሮ በመኖር ጌታን የማክበር ጥሪ አላባቸው።

***ድካምን በማገዝ አብሮ መኖር ፦***

“ደካማ ፍጥረት” ስለሆኑ ከሚለው ሀረግ ባሎች የሚስቶቻቸውን ጉድለት የመሙላት አደራ እንዳለባቸው እናያለን። “ደካማ ፍጥረት” ሲል ሚስቶች የስሜት፣ የጉልበት እና የቁሳዊ ነገሮችን መሻታቸውን ለመሙላት እገዛን እንደሚሹ ያሳያል። ይህ ለባሎች ማንም ሳያሳስባቸው በየዕለቱ ሊፈጽሙት የሚገባ አደራ ነው።

***በማስተዋል አብሮ መኖር፦***

በማስተዋል አብሮ መኖር ሚስት ያላትን መሻት፣ የልቧን ትርታ በመረዳት ለካስ ይረዳኛል፤ በደንብ ያውቀኛል፤ እስከትል ድረስ ድካሟን ማገዝና መሙላት ነው። ይህ አይነቱ አኗኗር ጤናማ የሆነ የህይወት ዘይቤ ነው።

***በአክብሮት አብሮ መኖር፦***

ሚስት ራሷን ስላአስገዛች የተናቀች አይደለችም። ሚስት በባሏ የተከበረች ነች። ሲያከብራት ለስሜቷ ይጠነቀቃል። ሃሳቧን ይቀበላል። ፍላጎቷን ለማሞላት ይተጋል። ለምን ሊያከብራት እንደሚገባው እንደሚከተለው እናያለን፣

1. አብራው የሕይወትን ጸጋ ወራሽ ስለሆነች። ሚስት የእግዚአብሔርን መንግሥት የምትወርስ በጌታ ዘንድ ሥፍራ ያላት ስለ ሆነች ባል ያከብራት ዘንድ ይገባል። ከዚህ መረዳት የተነሳም ያከብራታል።
2. ጸሎት እንዳይከለከል። ሌላውን መናቅና መግፋት የጌታን ፊት ለማየት ድፍረት አይሆንም። አብረናት ህይወትን የምንካፈላትን የትዳር ጎዳኛችንን እየገፋን ለጸሎታችን መልስን እናገኝም።

ባል የጌታን ፍቃድ የሚፈጽመው ሚስቱን በማስተዋል ድካሟን እያገዘ፣ እያከበራት አብሯት ሲኖር ነው። አብሮ መኖር ቤታቸውን ከብዙ አደጋ ይጠብቃል።

## በረከትንና መልካሙን የሚያይ ህይወት (1ጴጥ 3:8-12)

ይህ ክፍል “በመጨረሻ” በሚል ቃል ማጠቃለያና የሚቀጥሉትን ክፍሎች የሚያይዝ ምክሮችን ይስጠናል። በዚህ ክፍል ለበረከት የተጠራ ህይወት ልምምድ ምን

እንድሚመስል እንመለከታለን። በክፍሉ የተጠቀሱ ነጥቦች በቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጭ አማኝ ሊለማመዳቸው የሚገቡ እውነቶች ናቸው።

### ሀ. ለበረከት የተጥራ ህይወት ምን ይመስላል?

1. በአንድ ልብ ይሆናል/ይኖራል (1ጴጥ3:8፤ ፊል 2:1-11)
   ይህ አባባል ጽኑ ህይወት፣ የመንፈስና የአስተሳሰብ አንድነትን ያሳያል። አንድ ልብ የሚያስፈልገን፣ ለአመጽ ጉዳይ ሳይሆን አብ ለሚፈቅደው የተቀደሰ ጉዳይ ነው። [አንድ ልብ በሐናኒያና ሰጲራ ህይወት ታይቷል፤ ግን ልክ አልነበረም።] ነገር ግን መልካሙ አንድነት ቤታችንን ለመሥራት እጅግ አስፈላጊ ነው።
2. የሌላው መከራ ተሰምቶት ያግዛል (1ጴጥ 3:8)
   የወንድሞቻችን መከራ እንደራሳችን ሆኖ ሊሰማን ይገባል። የጌታን ፍቃድ ከምንፈጽምበት መንገድ አንዱ በመከራ ያሉትን ማገዝ ነው። አንድ ቤተሰብ ስለሆንን የሌላው ችግር እንደ ችግራችን ሆኖ ሊታየን ይገባል። የማይታየን እንኖር ይሆን? [1ጴጥ 1:22፣ 4:8፣ 5:14፤ 1ተሰ. 4:9፡ ሮሜ 12:15]
3. በወንድማማች መዋደድ ይዋደዳል (1ጴጥ 3:8)
   መጽሐፍ ቅዱስ ህግ ሁሉ በፍቅር እንደሚጠቀለል ያስተምራል (ሮሜ 13:8-10)። በማንኛውም የህይወታችን ገጽታ ላይ ፍቅር ገኖ መታየት አለበት። ጴጥሮስ የወንድማማች መዋደድ የተጠራንለት ህይወት መሆኑን ይናገራል። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 13 የፍቅር ዕዳ ብቻ እንዲኖርብን መናገሩ መዋደድ ቸል የሚባል ነገር አለመሆኑን ያመለክታል።

4. **የርኅራኄና የትህትና ህይወትን ያሳያል/ይለማመዳል (1ጴጥ 3:8)**
   ርኅራኄ ለሌላው የሚደርስ የተባረከ ባህርይ ነው። ርኅራኄ ለትዳር ጎደኞችን፡ ለወገኖች በሁኔታዎች ሁሉ እንድንቆምላቸው የሚያነሳሳና የሚገፋ የውስጥ ማንነት/ኃይል ነው።
   ትህትና በሌላው በኩል ከእኔ ይልቅ ሌላው ይሻላል ብሎ የሚቆጥር ዝቅ የማለት ጉልበት ነው። ትህትና ብርታትና ድካሙን ያለኩራት ወይም ያልዝቅተኛነት መንፈስ በትክክል የመጠቀም ጸጋ ነው።
   ርኅራኄና ትህትና በአንድነት በአማኝ ህይወት ውስጥ ሲንቀሳቀሱ መቀባበል፣ መተሳሰብ እና ሰላም በቀላሉ በግኑኝነቶቻችን ሁሉ ይታያሉ።

## 5. በደልን አይቆጥርም ይቅር ይላል፤ ደግሞም ይባርካል (1ጴጥ 3:9)

*ሥጋ እንዲህ ከአደረከብኝ እንዲሁ አደርጋለሁ ይላል። ምናልባትም ከዛ የከፋ "ዓይን ለዓይን ጥርስ ለጥርስ" የሚል አቋምን ይመርጣል። በአማኝ ያለው መልካሙ መንፈስ ግን በደልን አይቆጥርም፤ ይባርካል። ይህን በማድረግም "እንዲሁም" የሚለውን ምክር፣ ማለትም የክርስቶስን ፈለግ ይከተላል። የሰይጣን አሳብ ደግሞ መልካም ለአደረጉለት ክፋትን መመለስ ነው።*

**ለ. ለበረከት የተጠራ ህይወት ምን ያደርጋል?** (1ጴጥ 3:10-12)

ሰው ሁሉ ህይወትንና መልካም ነገርን ይፈልጋል። ግን በምን ሁኔታና እንዴት የሚለው ጉዳይ ይለያዩናል። ህይወትንና መልካሙን ቀን ለማየት ጴጥሮስ የሚስጠን ጥቂት ግን የከበሩ ምክሮችን አሉ።

1. ***አንደበትን መግዛት፡-*** "． ． .መላሱን ከክፉ ከንፈሮቹንም ተንኰልን ከመናገር ይከልክል" 1ጴጥ 3:10 [ያቆ. 3፤ መዝ. 141:3። ምን ይደርስብኛል ከማለት ሳይሆን ክፋትንና ተንኮልን ከመጥላት የተነሳ አንደበትን መግታት ተገቢ ነው።
2. ***ክፉን ሳይሆን መልካሙ ማድረግ፡-*** "． . .ከክፉ ፈቀቅ ይበል፥ መልካምንም ያድርግ፥" ( 1ጴጥ 3:11)

ከክፉ መራቅ አንድ ነገር ነው፤ መልካሙን ደግሞ ማድረግ ሌላ ነው። በተለያየ ምክንያት ሰው ክፋትን ከማድረግ ራሱን ይጠብቃል፣ ክፋትን ጠልቶ ግን መልካሙን ማድረግ የአማኝ ህይወትና ጥሪ ነው። ይህ የክርስቶስን ፈለግ መከተል ነው።

3. **ሰላምን መሻትና መከተል፡-** "． ． .ሰላምን ይሻ ይከተለውም፤" (1ጴጥ 3:11)።

ሰላምን መሻት ተገቢ ነው። መሻት ብቻ ግን በቂ አይደለም። ሰላምን መከተልም ይገባል። መሻቱና መከተሉ በአንድነት ሁሌ በአማኝ ህይወት ውስጥ የሚታዩ ናቸው። ብቻ አይድረሱብኝ ወይም እኔ ሰው ጋ አልደርስም ብቻ በቂ አይደለም። ሰላምን መሻታችንና መከተላችንን እንደድካም ቢታይም፤ አንዳንዴም ከዚህ አቋማችንን የተነሳ ሌሎች ቢጠቀሙብንም፣ ሁሌ በዚሁ መጽናት አለብን።

ለምን? ጸሀፊው የሚከተሉትን ነጥቦች ይሰጠናል፡-

**ሀ. የጌታ ዓይኖች ወደ እኛ ስለሚመለከቱ**

**ለ. ጆሮቹ ለጸሎታችን የተከፈቱ ስለሆኑ**

**ሐ. የጌታ ፊት ግን ክፉ በሚያድርጉ ላይ** ስለሆነ

እነዚህ ምክሮች ጌታ መከራ ውስጥ እንኳን አብሯቸው ስላለ መጽናት እንዳለባቸው ያስተምራል።

## መደምደሚያ

መከራ ውስጥ ህያውና ዘላለማዊ ተስፋ እያሰቡ ቤተሰብን በጌታ ፍቅር አብሮ መምራት ለከበረ ለእግዚአብሔር መንግስት ብቁ ያደርገናል። ለባልና ለሚስት በማንኛውም የህይወት ውጣ ውርዶች የክርስቶስን ምሳሌ መከተል ራስን ከመዳን አልፎ ሌሎችም እንዲድኑ መንገድ ይሆናል። ጌታም ዓይኖቹ ሁል ጊዜ ከእኛ ጋር እንደሆነ ማወቅ አለብን። ስለዚህ የተቀደሰ ኑሮ መኖር አለብን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. 1ጴጥሮስ 3፡ 1 እና 7 ላይ "እንዲሁም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምንድን ነው? እንዴት ነው ለሚስቶችና ለባሎች ከሚሰጠው ምክር ጋር የሚገናኘው?
2. 1ጴጥሮስ 3፡ 1-2 ላይ ለሚስቶች የተሰጠ ትዕዛዝ ምንድን ነው?
3. "**ተገዙ**" ማለት ምን ማለት ነው? በባለፈው ጥናት ይህን ቃል አንስተን ነበር? በምን ሁኔታ ነው ያነሳነው?
4. 1ጴጥሮስ 3፡3-4 በማንበብ የተረዳችሁትን አብራሩ
5. ሚስት ለባል ለምንድን ነው የምትገዛው? ክፍሉ ምን ያመለክታል?
6. አይሁንላችሁና ይሁንላችሁ የሚለው ስለምንድን ነው? ምንስ ማለት ነው?
7. 1ጴጥ 3፡5-6 ለሚስት የማንን ህይወት ነው እንደምሳሌ ያቀረበው? ሚስቶች እንዴት ነው ምሳሌውን የሚከተሉት? ፍሬውስ?

**ጊዜ ካልበቃ እዚህ ጋ ማቆም ትችላላችሁ**

8. 1ጴጥ 3፡ 7 በጌታ ፍርሃት ባሎች ከሚስቶቻቸው ጋር እንዴት እንዲኖሩ ነው የታዘዙትና የተመከሩት? ምክንያቶቹን ተወያዩባቸው።
9. 1ጴጥ 3፡ 8ና 9 ለበረከት የተጠራ ህይወት እንዴት ነው የተገለጸው?
10. 1ጴጥሮስ 3፡10-12 ህይወትን የሚወድና መልካሙን ቀን ሊያይ የሚወድ ሰው ምን ያደርጋል?
11. ሰላምን መሻትና መከተል ማለት ምን ማለት ነው? ይህን በህይወትህ እንዴት እንደምትለማመድ ምሳሌ ስጥ።

12. ሰላምን በመሻትና በመከተል መኖር ያለብን ለምንድን ነው? ክፍሉ የሚስጠንን ሦስት ምክንያቶችን ዘርዝር።

13. የጌታ ዓይኖች፣ ጆሮዎች እና ፊትን ከምን ጋር ነው ያያዛቸው? ምንስ ያመለክቱናል?

14. ከዚህ ጥናት በግላችን ምን ተማርን? እናካፍል።

## ጥናት ሰምንት
## የንባብ ክፍል 1ጴጥ 3:13-22
## “ክብር የሚገባውን የማክበር ህይወት”

**ዓላማ፡-** ጌታን ለማክበርና ተቃዋሚዎችን ለማሳፈር በጎ ህሊና እና መልካም ኑሮ ሊኖረን እንደሚገባ ማሳሰብ።

**መግቢያ፡-** ክርስትና አንድ ብቸኛ የሆነውን ጌታን የመከተል ህይወት ነው። የጌታን ፈለግ እየተከተልን መመላለስ ቀላልም ከባድም ነው። ቀላል የሚይደርገው እርሱ ምሳሌ ብቻ ሳይሆን በጉዞችን አብሮን መሆኑ ነው። ከባድ የሚያደርገው የእርሱ ፈለግ ከሥጋና ከአለም መርህ ጋር የሚጋጭ መሆኑ ነው። በዚህ ክፍል ጌታን በልባችን ስለመቀደስና እግዚአብሔርን በማክበር ምሳሌ ስለሆነን ሰው ህይወት በአጭሩ እንመለከታለን።

### በመከራ ውስጥ ስናልፍ ክርስቶስን በልባች አናንግስ፣እንቀድስ፣እናክብር 1ጴጥ. 3:13-17

እግዚአብሔርን እያከበርን ለመኖር ስንጥር እንቅፋት የሚሆኑብን ነገሮች አይጠፉም። ጽድቅን በመረጥን ቁጥር ዋጋን እንከፍላለን፤ ዓለም እና ሰይጣን ኑሮን ሊያከብዱብን ይነሳሉ። አማኞች መገንዘብ ያለብን፣ መከራ ምንም ቢበዛም ሊፈራ የሚገባን ስለምንፈራ በመጨርሻ ድል የእኛ መሆኑን ነው።

**1ጴጥ** 3:13-17 ጌታን እንዴት እንደምናከብር ጥልቅ የሆነ ምክርን ይሰጠናል።

**ሀ. በሚታይ ነገር ጌታን መባረክ (1ጴጥ 3፡13-15፣ 17፤1ጴጥ. 2:21)**

1. **በጎንና ጽድቅን በማድረግ፡-** ዋጋ ቢያስከፍልም፤ አማኝ ጌታውን ለማክበር ይህን አይነት ህይወት ይለማመዳል፤በዚያም ሌሎች በጌታ ህይወትን ሊያገኙ ይችላሉ።
2. **በግፍ መከራን ስንቀበል በመጽናት**፡- የተባረከውን ተስፋ መርጦ ዋጋ መክፈል የአማኝ ህይወት ነው። በጽድቅ እየኖሩ መከራን መቀበል አለ። ብድራት ግን አለው። አመጽን ፈጽሞ መከራ ከመቀበል በግፍ መከራን መቀበል ይሻላል። ቃሉ “ስለ ጽድቅ መከራን ብትቀበሉ ብፁዓን ናችሁ” ይላል።

3. **ለሚቀርብልን ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በመዘጋጀት፡- ምን በማድረግ ?**
   - አማኝ የተጠበቀለትን ተስፋ በመለየት
   - አማኝ ምላሹን በየዋህነትና በፍርሃት መንፈስ በማቅረብ ያሳያል

**ለ. ተቃዋሚዎችን የሚያሳፍር ህይወት መኖር** [ሀሰትን መሰረተ አልባ የሚያደርግ ኑሮ] ***(1ጴጥ 3፡16፣17)***

- በክርስቶስ በመሆን ያለውን መልካም ኑሮ መኖር
- በበጎ ሕሊና በመመላለስ
- የጌታን ፍቃድ በማከናወን

## ድል የነሳው ጌታና ሥራው 1ጴጥ. 3:18-22

1ጴጥ. 3:18-22 ጌታ በሞቱ ለህያዋንና ለሙታን ስለ አከናወነው የማዳን ሥራ እና አሁን ሳለለበት የማዕረግ ሥፍራ ይናገራል። ይህ መልዕክት ደግሞ በዚያን ወቅትም ይሁን አሁን በመከራ ውስጥ እያለፉ ለነበሩና ላሉም ምሳሌና ብርታት ነው። ክፍሉ በጣም አወዛጋቢ አሳብን ያዘለ ነው። ቢሆንም በምዕራፉ መሰረታዊ አሳብ ላይ በማተኮር እንመለከታለን። በመጀመሪያ ባልና ሚስት የክርስቶስን ፈለግ በመከተል በቤታቸው እንዴት እንደሚመላለሱ ተመልክተናል። በመቀጠል ጌታን በልባችን ስንቀደስና በህይወታችን ስናከብረው ስለሚደርስብን ሰልፍ ተመልክተናል። የምዕራፉ መዝጊያ የክርስቶስ ህይወት የአብን ፍቃድ ከፈጸመ በኃላ እንደከበረ ያሳያል። ይህ ጌታ ምን አደረገ? የተደረገላቸውስ?

1. ጻድቅ ሆኖ ለዓመፀኞች በዓመፀኞች ተገፋ (1ጴጥ. 3:18፣ 22)
   - **ዓላማው፡-** ወደ አብ ያቀርበን ዘንድ ነፍሱን ሰጠ። ስለእኛ በደል ሲል አንድ ጊዜ፣ለአንዴና ለመጨረሻ፣ ሞተልን።
   - ***በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፡-*** ምን ማለት ነው? ይህ አባባል ብዙ ዓይነት አተረጓጎምን አስከትሎል። አንድ እውነት ግን ግልጽ ነው። ይታደገን ዘንድ ያለፈበትን ወቅትና አሁን ያለበትን የድል ዘመን ያሳያል።
     - “በሥጋ ሞተ . . .”፡- የሰው ልጅ የሞት ፍርድ አለበት። ይህን ፍርድን ያነሳልን ዘንድ ጌታ ሥጋን ለብሶ ሞታችንን እንደሞተልን ይህ ሀረግ ያሳየናል። አንዘንጋ እርሱ ሥጋን ለብሶ ሞታችንን እንደሞተ በማሰብ ምስጋናን እናጎድል።
     - “በመንፈስ ግን ሕያው …”፡- ድል ነስቶ በክብር መቀመጡን ነው የሚያመለክተን። በግዑዙ አለም በአካል ተወስኖ ሳይሆን በከበረ

ሁኔታ በድል የመኖሩና ሁሉ ቦታ የመገኘቱ መግለጫ ነው። ሞት ይዞት አልቀረም፤እርሱ ተነስቷል! አሁን ሕያው ሆኖ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ።

2. የማዳን ሥራው የአዳም ልጆችን ሁሉ ያካትታል (1ጴጥ. 3:19-20)

እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ብዙዎችን አከራክረዋል፤ ያከራክራሉም። **"በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት"** ሲል ምን ማለቱ ነው? ምንድንስ ነው የሰበከላቸው? ስለኖኅ የሚጠቅሰው ለምንድን ነው? እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ጥያቄዎችም ከክፍሉ ይነሳሉ። እንደ ጥያቄዎቹ አስቸጋሪነት የአተረጓጎም ልዩነቶች እንዳሉ ልንገነዘብ ይገባል።

በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ሥፍራ፣ መልዕክትና ሰለ ሰው ልጆች ምላሽ ከታሪክ ውስጥ ምሳሌን እንመለከታለን (የኖህ ጊዜ ታሪክ)።

***ሥፍራ***፡- አንድ እውነት በየትም ቦታ በምድር ይሁን፣ በሲኦል ይሁን፣ በሰማይም የጌታ የማዳን ሥራ ሊነገር ይገባል።

- በህይወት ላሉ፡- በጌታ ለሚያምኑ ጽኑ የድህንነት ተስፋ፤
- በሞት ላለፉ፡- በእምነትና በመታዘዝ ያሳለፉት ህይወት መና እንዳልቀረ ፍጻሜ በሚሰጠው ጌታ ሙላትን እንዳገኘ ያሳያል

**መልዕክት**፡- በደፈናው ሰበከላቸው ስለሚል የራሱን ሥራ ካልሆነ ሌላ መልክት አይኖርም። ስለዚህ "ተፈፀመ" በማለት የተናገረ ጌታ፤ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ምህረትን በሞቱ መቀበሉን፤ ባለማመን ደግሞ ፍርዱ እንደተቆረጠ ያሳያል። በእርሱ ሥራ ለአመኑ ህይወት፣ ላላማኑ ፍርድ ታወጀ።

**በታሪክ የተገለጸ ምላሽ፦** ለ120 አመት በኖኅ ስለሚመጣው ፍርድ ግድ ያልነበራቸው ብዙዎች እንደነበሩ፤ ዛሬም ለብዙዎች የመዳን መንገድ ሞኝነት ነው። ብራ ነው እንዴት ዝናብ ይመጣል ብለው በውኃ እንደጠፉ፤ በዘመናት ሁሉ ለደኅንነት ወንጌል ተገቢውን ምላሽ ሳይሰጡ የጌታ ፍርድ የሚያገኛቸው ብዙዎች ናቸው። ይህ እጅግ ጠቃሚ ትምህርት ነው። ኖኅ ዘመን የጠቀሰው፣ የጌታን ትዕግስት የሚያቃልሉን ለማስጠንቀቅ ነው። አሁንም በዚህ ዘመን እንደዚሁ መሆኑን ማወቅ አለብን።

3. በእርሱ ያሉ የመታዘዝን ፍሬ ያሳያሉ (1ጴጥ. 3:21-22)

በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች መካከል የአተረጎጎም ልዩነት ብቻ ሳይሆን የእምነት መሰረት ልዩነትንም የፈጠረ ክፍል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ

የሚቃረን ሀሳብን አያስተላልፍም። ስለዚህ ግራ የሚያጋባንን ክፍል ልንረዳ የምንችለው ሌላ ሥፍራ ግልጽ ሆኖ ከተሰጠን አሳብ ጋር በማዛመድ ነው። የክፍሉንም ሙሉ ሀሳብ ማየቱ እጅግ ጠቃሚ ይሆናል።

ቁጥር 21 ላይ **“. . .ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል፥. . .”** የሚለውን በመጥቀስ ጥምቀት እንደሚያድን የምያስተምሩ የስህተት አስተማሪዎች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ መዳን በማንም እንደሌለ፤ ድኅነት በክርስቶስ የማዳን ሥራ ብቻ መሆኑን አስረግጦ ያስተምራል። ለዚህ ሙሉ የዮሐንስ ወንጌል በቂ ትምህርት አለው። ስለዚህ ይህ ሀረግ ከኃጢያት ፍርድ ማምለጫ ብቸኛ መንገድ አደለም። በማርቆስ 16፡ 16 ያልተጠመቀ ይፈረድበታል አይልም፣ ያላመነ እንጂ “16 ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል”።

**“የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም፥” እና “ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ”** የሚሉትን ሀረጎች ስንመለከት አንድ መሰረታዊ ጉዳይን እናስተውላለን። አማኝ ጌታውን በልቡ የመቀደስና በበጎ ሕሊና መመራት ባህርይው መሆኑን ነው። ይህም የትንሣኤ ፍሬ ነው።

ስለዚህ ጥምቀት ያድነናል ሲል፤ ራሳችንን ለጌታ መለየታችን የምንገልጽበት ምሳሌያዊ ሥርዓት መሆኑን ብቻ ነው የሚያሳየን። አማኝ የድብቅ ኑሮ በመኖር በሁለት ዓለም ነፍሱን አያስጨንቃትም። የምንድነውም ጠፊዋ ዓለም ልጆቿን ከምትመራበት የሞት መንገድ ነው።

በተለይ ጴጥሮስ ለሚጽፍላቸው በብዙ መከራ ለሚያልፉ ጥምቀት የጌታ መሆናቸውን የሚገልጹበት ሥርዓት ነበር።

## *መደምደሚያ*

በመጨረሻ ድሉ ወንጌልን ላመነ ሰው ነው። ይህን ድል ለማግኘት ልዩ ልዩ አይነት መከራ ሲገጥመን ተስፋ እንዳለው ሰው በሥጋው ሞቶ ኃጢአታችንን ያስወገደልንን ጌታን በማሰብ ጸንቶ መቆም የህይወት ወራሾች ያደርገናል። በሌሎች ዘንድ ለጽድቅ መከራን በመቀበል እነርሱም አይተው ለህልናቸው እንዲፈርዱም በማድረግ ጌታን እንዲያገኙ እድል መስጠት የክርስቲያን ኃላፊነት ነው። ክርስቶስ ሞትን አሸንፎ በሁሉ ቦታ ይገኛል። በሁሉ ሥፍራ ሄዶ የድልን አዋጅ አወጀ። በኖህ ጊዜ የሆነው እውነት አሁንም እየሆነ ይገኛል፤በመጨረሻም ዘመን ፍርድ ይሆናል።

## *መወያያ ጥያቄዎች*

1. በ1ጴጥሮስ 3፡13-14 የሚመክራቸውና የሚጠይቃቸው ምንድን ነው?
2. ጌታን በልብ መቀደስ ማለት ምን ማለት ነው? ለምንስ አስፈለገ?
3. 1ጴጥሮስ 3፡ 15 ስናነብ ዘወትር ስለምንድን ነው የተዘጋጃችሁ ሁኑ የሚላቸው? በምን መንፈስ ነው ማከናወን ያለባቸው?
4. በ1ጴጥሮስ 3፡16-18 መሰረት ስለ ምንድን ነው ስድብና ሃሜት የሚገጥማቸው? ያገኛችሁትን እውቀት ተወያዩ።
5. ወደረኞቻቸውን የማሳፈሪያ መንገድ አድርጎ የሚመክራቸው ምንድን ነው?
6. የተሻለነው ብሎ የሚመክራቸው ስለምን ጉዳይ ነው? ለዚህስ የሚስጣቸው ምሳሌ ማነው?
7. ክርስቶስ ያደረገው ምንድን ነው? ፍሬውስ? (ቁጥር 18)
8. የኖህ ጊዜ ምሳሌ መጥቀስ ለእኛ ምን ይጠቅማል (ይህን ጥያቄ መመለስ ከስህተት ትምህርት ይጠብቀናል)? ከዛሬ ጥናት ምን ተማርን?

## *ተጨማሪ ማብራሪያ ለ1ጴጥሮስ 3፡19-21*

**በቁጥር 19,20 ላይ በርከት ያሉ አተርጎጎሞች አሉ። ሁሉንም ማየት አንችልም። የሚከተሉትን ነጥቦች ግን ልብ እንበል።**

●***ሥፍራ፡-*** በውኅኒ/በሲዖል ለነበሩ ሲል የሚለውን እንዳለ ከመውሰድ በስተቀር ለሌላ ትሩጓሜ የሚያበቃን ነገር አናገኝም። ሙታን ያሉበት

●**መልዕክት፡-** ሰበከላቸው ይላል። ምን እንደሰበከ ክፍሉ በግልጽ አይናገርም። መልዕክቱም የሰው ልጅ በማመን ከእግዚአብሔር ምህረት እንደሚያገኝ፤ ካላመነ ደግሞ ፍርድ እንደሚጠብቀው ያሳያል። በእርሱ ሥራ ለአመኑ ህይወት፣ ላላማኑ ፍርድን ያሳስባል። ጌታ ሁሉ ቦታ መገኘቱንና ድል ማወጁን እንጂ ሌላ የድነት እድል መስጠቱን አያሳይም።

●**የኖኅ ዘመን ምሳሌነት፡-** በኖህ ዘመን አመጽ ሰፍኖ ነበር፤ የኖህን መልዕክትም አልተቀበሉም ነበር። እግዚአብሔርም በትዕግሥት ህዝቡም ባለመታዘዝ ህይወት

ነበሩ። የኖኅ ዘመን የተጠቀሰው፣ የጌታን ትዕግስት የሚያቃልሉትን ለማስጠንቀቅ ነው። **“ነፍሳት”** የሚለው ቃል ብዙ ትርጉም ቢኖረውም ብዙዎች እንደሚሉት በኖህ ጊዜ የሞቱትን ሰዎች ያሳያል።

**●ጥምቀት ያድናል ወይስ አያድነንም?** መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ መዳን በማንም እንደሌለ፤ ድኅነት በክርስቶስ የማዳን ሥራ ብቻ መሆኑን አስረግጦ ያስተምራል (ሐዋ 4፡12)። ስለዚህ ይህ ሀረግ ከኃጢያት ፍርድ ማምለጫ መንገድ አይደለም። ስለዚህ ጥምቀት ያድነናል ሲል፤ ራሳችንን ለጌታ መለየታችንን የምንገልጽበት ሥርዓት መሆኑን ነው የሚያመለክተው። አማኝ የድብቅ ኑሮ በመኖር በሁለት ዓለም ነፍሱን አያስጨንቃትም። የምንድነውም ጠፊዋ ዓለም ልጆቿን ከምትመራበት የሞት መንገድ ነው። ጥምቀት ኃጢአት የሞት ቅጣት ማግኘቱንም ምሳሌ ሆኖ ያሳያል። ስለዚህ መልሱ አያድነንንም ነው።

## ጥናት ዘጠኝ
## የንባብ ክፍል 1ጴጥሮስ 4፥1-11

## እስከ መጨረሻ ዘመን ለጽድቅ መከራ በመቀበል ለመጽናት የክርስቶስን ምሳሌ በመከተል ኃጢአትን እናሸንፍ

ዓላማ፡- አማኝ በመከራ ውስጥ የክርስቶስን ምሳሌ በመከተል መጽናት እንዳለበትና መከራንም ፈርቶ ኃጢአት መሥራት እንደሌለበት ማሳወቅ።መከራ

**መግቢያ**፡-ለሁሉም ነገር መጨረሻና ፍርድ አለው። በጌታ የዳነ ሰው ለእውነት ብቻ መከራ መቀበል አለበት። በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣው መከራ እራሱ መጠበቅ የክርስትና ኃላፊነት ነው። ለዚህ ሁሉ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ያሳለፈው ህይወቱና አገልግሎቱ ለህይወታችን እጅግ ጠቃሚ መመሪያ ነው።

### 1ጴጥሮስ 4፥1-6 በጌታ የዳነና ያልዳነ ሰው ንጽጽር

**ሀ. 1ጴጥሮስ 4፥1-3 "..ያን አሳብ እንደ ዕቃ ጦር አድርጋችሁ ያዙት..."** ይህ "አሳብ" ብሎ የሚናገረው ምንድ ነው? በዚህ ክፍል በ1ጴጥ 3፥18 የተጠቀሰውን እንደገና በተዘዋዋሪ ይደግማል "ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" (1ጴጥ 3፥18)። **"እናንተ ደግሞ ያን አሳብ እንደ ዕቃ ጦር አድርጋችሁ ያዙት**" በማለት እንደ ጌታ ለጽድቅ መከራ እንድንቀበል ያስተምረናል። በርግጥ ለማጠንከር ብዙዎች ይህን ሃሳብ ከሮሜ 6፥13 ጋር ያገናኛሉ "ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም **<u>የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ</u>**" መከራን ፈርተን ለኃጢአት ራሳችንን አሳልፈን መስጠት አይገባንም ። **1ጴጥሮስ 4** ቁ.1 እና 2 ላይ እንደ ሥጋ ምኞት አትኑሩ የሚለውን ቁ.3 ላይ "የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበትን" ይላል። እነዚህን የአሕዛብን ፈቃድ ወይም የሥጋ ምኞቶች ያላቸውን ሰዎች ተግባራቸውን በሚቀጥለው ቁጥር ያብራራል። እነርሱም 1. **መዳራት** 2. **ስካር** 3.**ዘፈን** 4. **ጣዖትን ማምለክ** ናቸው። እነዚህ ኃጢአቶች እርስ በርስ የተገናኙ መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም ማለትም አንዱ ሌላውን ያስከትላል። በዚህ ክፍል አማኝን ለጦርነት የተዘጋጀ ወታደር አድርጎ ያቀርባል።

ማለትም ኃጢአትን ሊዋጋ የተዘጋጀ ክርስቲያንን ያመለክታል። የኤፌሶንን 6፡10-17 ያለውን የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ያስታውሰናል።

ኃጢአትን እየተለማመደ ያለ ክርስቲያን የሰይጣን መጠቀሚያ መሳሪያ ከመሆኑም አልፎ ህይወቱን የማጣት እድል ከፍተኛ ይሆናል። 1ጴጥ 2፡21-23 ጥሩ ምሳሌ ይነግረናል “21የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና።22እርሱም ኃጢአት አላደረገም፥ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤23ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፥ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤” ስለዚህ ክርስቲያን መከራ ውስጥ እንኳን ቢሆን ኃጢአትን ለማሸነፍ መታጠቅ አለበት እንጂ ወደነበረበት መመለስ የለበትም። ማወቅ የሚገባን ብዙ ሰዎች በምድር ላይ በተለያዩ መከራዎች ውስጥ ያልፋሉ። ኃጢአትን ግን ሊያሸንፉ አይችሉም:: ምክንያቱም ያለ ጌታ አይቻልምና። መከራ ሁሉ ስለ ክርስቶስ የሚመጣ አይደለም:: ፈሪኦን መከራ ቢበዛበትም ኃጢአት ግን እየጨመረ ሄደ እንጂ አልዳነም። አማኞች ስለ ጽድቅ መከራ ሲቀበሉ ለምን እንደሚቀበሉ ያውቃሉ፤የጌታም ጸጋ አላቸው።

## ለ. 1ጴጥሮስ 4፡4-6 በመጨረሻ ቀን ለሁሉም ዋጋና ፍርድ እንዳለው አማኝ ማወቅ አለበት

በዚህ ክፍል አማኞችን በክርስቶስ ካልሆኑ ሰዎች ጋር ያነጻጽራል። እነዚህ ክርስቲያኖች በነበሩበት ቦታዎች ህዝቡ በተለያዩ የሃይማኖት፣የፍልስፍና የባህልና የፖለቲካ ተቋማት የኃጢአት እውቀት የሌላቸውና እንደ ልባቸውና እንደ ድርጅቱ መመሪያ የሚኖሩ ነበሩ። ክርስቲያኖች ኃጢአትን እምቢ ሲሉ ይደነቃሉ።ለሥጋ ፍላጎት የማይመች አዲስ ትምህርት፣ አዲስ ኃይል ወይም አዲስ ነገር ነው። በመንፈስ ቅዱስ ሐዋ ጴጥሮስ እንደሚከተለው ይላል። ማንም መከራ ያምጣ መከራም ይቀበል ነገር ግን የሁሉም ሥራ በመጨረሻ ለፍርድ ይቀርባል ይላል ። “ግን እነርሱ በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ለተዘጋጀው መልስ ይሰጣሉ” 1ጴጥ 4፡5። ወንጌል ሲነገራቸው ቢቀበሉ እነርሱ እንኳን በመንፈሳቸው ህያዋን የመሆን ተስፋ ነበራቸው። ነገር ግን ጌታ ካልተቀበሉ በሥጋ እንኳን ቢኖሩ በመፈስ ሙታን ናቸው። **1 ጴጥሮስ 4፡.6** በጊዜው በክርስትና ምክንያት በሥጋቸው ዋጋ ተቀብለው የሞቱት እንኳን በመንፈስ በጌታ ዘንድ ህያዋን ናቸው የሚለውን ሀሳብ ይህ ቁጥር

እንደሚያብራራ ብዙዎች ይስማማሉ። በሥጋም በነፍስም በዓመጸኛውም በጻድቁም ጌታ ይፈርዳል። ስለዚህ በዚህ ታላቅ ተስፋ መጽናት አለብን።

## 2. 1ጴጥሮስ 4:7-11 ቀኑ ቅርብ ስለሆነ ክርስቲያን ሁልጊዜ በዚህ እውቀት መመላለስ አለበት

**"እንግዲህ እንደ ባለ አእምሮ አስቡ፣ ..."** ምንድን ነው እንደ ባለ አዕምሮ አስቡ እያለ ያለው? የመጨረሻ ጊዜ በተለይም የክርስቶስን ዳግም ምጽዓት መጠባበቅ የአማኞችን ዝንባሌ ድርጊትና ግንኙነት መልክ ያስዘዋል። እውቀት ያለው መንፈሳዊ ህይወት ለእድገት መሰረት ነው። ይህንን የመጨረሻ ዘመን በማሰብ እስከ ቁ. 11 ማሰብና ማድረግ ያለባቸውን ዝርዝር ነገሮችን ያብራራል 1. **ጸልዩ፡-** ትጸልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ (መጸለይ እንድትችሉ ከመጠን በላይ ለኑሮ አትጨነቁ)። ክርስቲያን ለጸሎት ትኩረት ካልሰጠ በየአቅጣጫው የሚመጡትን መከራዎች መቋቋም አይችልም። **2. ተፋቀሩ፡-** ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ ።ይህ የክርስትና ህይወት ማእከል ነው። ወንጌልን ለመስበክም ሰዎችን መውደድ መቻል አለብን። **3. ሌሎችን ተቀበሉ (ፍቅር ስሜት ብቻ ሳይሆን ተግባርም ነው)፡-** ያለ ማንጐራጐር እርስ በርሳችሁ እንግድነትን ተቀባበሉ፡- ይህ መልእክት ደግሞ ሊያብራራ የፈለገው በመከራ ውስጥ ያሉትንና የተቸገሩትን መርዳት የአማኞች ኃላፊነት መሆኑን ማወቅ ከመልዕክቱ ሀሳብ ጋር አብሮ ይሄዳል **4. አገልግሉ፡-** ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤ **ሀ) ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥** እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ **ለ) የሚያገለግልም ቢሆን፥** እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል (ከትዕቢትን በመጠበቅ) ፤ **ሐ) ለእግዚአብሔር ክብር አገልግሉ፡-** ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን። በጥቅሉ ሁሉም **ክርስቲያን በመናገርም ሆነ በማድረግ** እንደየጸጋው ለጌታ ክብር በመከራ ውስጥ ያሉትንም ሆነ ሌሎችን በቅንነት ቢያገለግል ጌታ ይመሰገናል፤እርሱም በመጨረሻ ሙሉ ዋጋ ያገኛል። ይህ ክፍል ከ1ቆሮ 12-14 እና ሮሜ 12 ጋር አንድነት ያለው ክፍል ነው።

## መደምደሚያ

መከራ የሰው ልጅ በኃጢአት ላይ እንዲጨክን እድገት ይሰጠዋል ወይም አማኝ ክርስቶስን ወደ መምሰል እየተቃረበ እንዲሄድ ያደርጋል።መከራን አብሮ ለመጋፈጥ መጸለይ፣መፋቀር፣ሌሎችን መቀበልና፣አንዱ ሌላውን በመከራ ውስጥ በልዩ ልዩ ጸጋ ማገልገል ያስፈልጋል። በምድር ላይ ማንም ሰው ለሚያደርገው ነገር በመጨርሻ ዘመን ፍርዱንና ዋጋውን ያገኛል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. 1ጴጥ 4፡1-3 አንብበን ምን እንደተረዳን እንወያይ። በተለይም "...ያን አሳብ እንደ ዕቃ ጦር አድርጋችሁ ያዙት..." የሚለው ሀሳብ ምንድ ነው? ያን አሳብ መያዝ ለምን ይጠቅማል?
2. 1 ጴጥ 4፡3 "የአህዛብ ፈቃድ" ብሎ ያለውን በዝርዝር ተወያዩ። እነዚህ የሥጋ ፈቃዶች በአሁን ዘመን አሉ? ስለ እነዚህ ነገሮች መነጋገራችን ለእኛ ምን ይጠቅማል?
3. ለምንድ ነው የተጠራነው? (መልሱ ግልጽና መብራራት አለበት)
4. 1ጴጥ 4፡4-6 አንብባችሁ የተረዳችሁትን አብራሩ። በዚህ ክፍል ስለ መጨረሻ ዘመን የሚናገር ነገር ካለ እንነጋገር።
5. የ1ጴጥሮስ 4፡7-11 ዋና ሀሳብ ምንድ ነው? ከቁ.4-6 ጋር ምን ግንኙነት አለው? ቁ.7 ትኩረት ይሰጥ።
6. በዚህ በ1ጴጥሮስ 4፡11 እንዲያደርጉ የተጠየቁትን ነገሮች ተወያዩ። ለመጨረሻ ዘመን ኑሮ ምን ጥቅም አለው?
7. ስለ ክርስቶስ ከመካከላችሁ ልዩ ልዩ መከራ የተቀበለ ሰው አለ? መስክሩ። ከሌላችሁም ስለሚታወቁት (በማንበብም ይሁን ከታርክ) ሰው መስክሩ።
8. በዓለም ላይ መከራ ስለሚቀበሉ ክርስቲያኖች ዛሬ ጸልዩላቸው (በተለይም በመካከለኛው ምስራቅና በሩቅ ምስራቅ ላሉት)።

# ጥናት አሥር

## የንባብ ክፍል 1ጴጥሮስ 4፡12-19

## አማኝ ስለ ጽድቅ እንጂ ኃጢአት በማድረግ መከራ መቀበል የለበትም

**ዓላማ፡-** የክርስቲያን መከራ በክርስቶስ መምጫ መጨረሻ ቀን ደስታና ክብር እንዳላው ማሳወቅ። በዚህም ምክንያት ክርስቲያን በሙሉ ተስፋ ክርስቶስን እያየ መኖር አለበት የሚለውን ትምህርት ማስጨበጥ።

**መግቢያ፡-** ዓለምን ሰዎች በኃጢአት ስለበከሏት ዓለምና ሰይጣን በሰው ዙሪያና ውስጥ በመሆን በክርስቶስ ተከታዮች ላይ መከራ ያበዛሉ። ጌታ እንደተናገረ በዓለም ላይ ክርስቲያን መከራ አለበት "… በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐ 16፡33) ። ንጉሥ ኔሮ ያስነሳው መከራ በጊዜው ለነበረው ቤተ ክርስቲያን ከባድ ነበር። ሁሉም የየራሱ መከራ አለው፣ግን ለወንጌል መሆን አለበት። መታወቅ ያለበት መከራ የክርስቲያኖች መጨረሻ እንዳልሆነ ነው። የክርስቲያን መከራ ዋጋ አለው። ይህንን እውነት በዚህ ጥናት እናያለን።

1. **1ጴጥ 4፡12-14 እንደ እሳት በሚፈትን መከራ ውስጥ ደስ ይባላችሁ** (ማቴ 5፡10-12 ይነበብ)

ክርስቲያን እንደ እሳት ከባድ በሆነ መከራ ውስጥ ሲያልፍ እንዴት ደስተኛና ብጹዕ ሊሆን ይችላል? እነዚህ ቁጥሮች በጊዜው ለነበሩ ወይንም እስካሁን ድረስም ላሉ ክርስቲያኖች ክርስቲያናዊ መከራ የመጨረሻ ዘመን ተስፋ፣ደስታና ክብር ያለው ነገር እንደሆነ ይናገራል። መከራ አብረን ለዘላለም የምንኖርበት ነገር አይደለም። በመከራ ውስጥ ዘላለማዊ ድስታ አለው። ደስታውም ሊሆን የሚችለው የዚህን ምድር ስኬት ብቻ እያሰቡ መደሰት ሳይሆን በሚመጣው ዓለም በእግዚአብሔር መንግስት ስለሚገኘው ክብርና ተስፋ በየዕለቱ በማሰብ ነው (ማቴ 24፡30፣25፡31) ። የክርስቶስ መንፈስም በየቀኑ የሚያበረታ ኃይል ነው። እንደውም መከራ ውስጥ ሲታልፉ "አትደነቁ" ይላል ለምን ለሚለው መልሱ ቁ.14 ላይ ተጠቅሷል " 14 ስለ

ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ” ይላል። ወዳጆች ሆይ ምንም ባይመቸን የክብር መንፈስ ከኛ ጋ ይሆናል። የዕብ 11 የእምነት ጀግኖች ምሳሌያችን ይሁኑ። ጌታም ምሳሌያችን ነው።

## 2. 1ጴጥ 4፡15-16 ክርስቲያን መከራ መቀበል የሌለባቸው ነገሮች፤ራሳችን የምናመጣውና ጌታን የማያስከብር መከራ፡-

ሐዋ ጴጥሮስ በሚከተሉት ነገሮች ምክንያት ክርስቲያን መከራ መቀበል የለበትም ብሎ ይናገራል። ማለትም ጌታ የማይፈቅዳቸውን ኃጢአት የሆኑ ነገሮችን በማድረግ መከራ መቀበል የለበትም። ለምሳሌ:- 1. **ነፍሰ ገዳይ** በመሆን 2. **ሌባ** በመሆን 3. **ክፉ አድራጊ** በመሆን እና 4. **በሌሎች አላስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች** በመግባት መከራ መቀበል የለበትም። በጽድቅ መከራ ቢቀበል ግን ጌታችን ክብሩን ይወስዳል “ሎሌዎች ሆይ፥ ለበጎዎችና ለገሮች ጌቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለጠማሞች ደግሞ በፍርሃት ሁሉ ተገዙ።በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ሀዘንን ቢታገሥ ምስጋና **ይገባዋልና። ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጎሰሙ ብትታገሡ፥ ምን ክብር አለበት?** ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ፥ ይህ ነገር በእግዚአብሔር **ዘንድ ምስጋና ይገባዋል”**(1ጴጥ 2፡18-20)።

“በጎንም ለማድረግ ብትቀኑ የሚያስጨንቃችሁ ማን ነው? ነገር ግን ስለ ጽድቅ እንኳ መከራን ብትቀበሉ ብፁዓን ናችሁ። ማስፈራራታቸውንም አትፍሩ አትናወጡም፥ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። ... በክርስቶስ ያለውን መልካሙን ኑሮአችሁን የሚሳደቡ ሰዎች ክፉን እንደምታደርጉ በሚያሙበት ነገር እንዲያፍሩ በጎ ሕሊና ይኑራችሁ ። የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲህ ቢሆን፥ ክፉ ስለ ማድረግ ሳይሆን በጎ ስለ ማድረግ መከራን ብትቀበሉ ይሻላችኋልና” (1ጴጥ 3፡13-18)። ቁ.16 ክርስቲያን ግን ስለ እግዚአብሔር መከራ ቢቀበል በድፍረት ሳይፈራ ጌታን ሊያመሰግን ይችላል። ጌታም ከእርሱ ጋር ይሆናል (ዳናኤልንና ጓደኞቹን አስቡ)። ሰው በከንቱ መከራ ሊቀበል ይችላል። በከንቱ መከራ ሊቀብል ክርስቲያን

አልጠራም። የምናደርገውን ሁሉ ማወቅ አለብን። በመከራ ውስጥ የጌታ ክብር በእኛ ሲገለጥ ጌታ የማያምኑ ሰዎች ጌታን ሊቀበሉ ይችላሉ።

### 3. 1ጴጥሮስ 4፡17-19 ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን? የመጨረሻ ዘመን አስፈሪ ነው።

በ20ኛው ክፈለ ዘመን ከተነሱት የስህሰት ትምህርቶች አንዱ "እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ የሰውን ዘር ሁሉ ይቅር ይላል፤ጨክኖም አያጠፋም፤ ስለዚህ በየትኛውም ሀይማኖት ይመን የሰው ልጅ ወደ ሲዖል አይሄድም" የሚል ነው።፡ነገር ግን ይህ ክፍል እንደሚነግረን ለሁሉም ፍርድ እንዳለ ነው። ለክርስቲያን ፍርዱ አሉታውም አዎንታውም ሊሆን ይችላል። ያመኑ ለሚመስሉና ላላመኑትም ሆነ ፍጹም ላላመኑት ፍርዱ ያው ነው (ማቴ 7፡22)። እግዚአብሔር ጻድቅ ነው። በርግጥ ማወቅ የሚገባን ክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ እያለ ባደረገው ኃጢአት ላይ ክርስቶስ በመሞት በምትክ ተቀጥቶ የኃጢአቱን ዋጋ አግኝቷል። ክርስቶስን ለተቀበሉት የኃጢአት ቅጣት ፍርዱን ካገኘ ያላመኑት መጨረሻቸው እንዴት የሚያስፈራ ይሁን። የተከፈላቸውን የኃጣትን ዋጋ ስላላመኑ የእምቢተኝነታቸውን ዋጋ ይቀበላሉ።

በመከራ ውስጥ ክርስቲያን ከፍርድ ለማምለጥ እስከሞት ቆራጥ መሆን አለበት፤ጌታም ችሎታው ሰማይና ምድርን እስከሚፈጥር ስለሆነ በጌታ ታምኖ መከራ መጋፈጥ ነው (1ጴጥሮስ 4፡19)። ብንሞት እንኳን ነፍሳችን በእርሱ እጅ ትሆናለች። መከራና ሞት በክርስቲያኖች የሚያመጡ ሰዎች የክርስቲያኖችን ከሥጋቸው በስተቀር በነፍሳቸው ላይ ምንም ዓይነት ሥልጣን የላቸውም።

### መደምደሚያ

የጌታ ሰዎች መጨረሻቸው በዚህ ምድር የሚጋፈጡት መከራ አይደለም። መቀበል ያለባቸው መከራዎች ግን ስለ ጌታ ብለው እንጂ በራሳቸው ድክመት የሚያመጡት መሆን የለበትም።ክርስቲያን ነፍሱን እስኪሰጥ ስለጌታ መከራ እንዲቀበል ተጠይቋል። የነፍሱም ባለቤት ጌታ አለ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. 1 ጴጥሮስ 4፡12-13 በማንበብ ዋና ነጥብ ተወያዩ። አንድ አማኝ እንዴት በመከራ ሊደሰት ይችላል? “ክብሩ ሲገለጥ” ማለት ምንድ ነው፤መቼ ነው ይህ የሚሆነው?
2. 1 ጴጥሮስ 4፡13 አንድ በመከራ ውስጥ እያለፈ ያለ ክርስቲያን እንዴት ብጹዑ ሊሆን ይችላል? ብጽዕናና መከራ ምን ይገናኛል?
3. 1 ጴጥሮስ 4፡14 ላይ መከራ አትቀበሉ ብሎ የሚመክራቸውን ነጥቦች በዝርዝር ተነጋገሩ።በነዚህም ነገሮች ምክንያት መከራ የሚቀበሉ ሰዎች አሉ ማለት ነው?
4. ስለ ዳንኤል፣ ስለ ጓደኞቹና ስለመርዶክዩስ ተወያዩ። ከእነርሱ ህይወት ምን እንማራለን?
5. 1 ጴጥሮስ 4፡14-16 አንብባችሁ፣የተረዳችሁትን አካፍሉ?
6. 1 ጴጥሮስ 4፡17-19 በማንበብ ያገኛችሁትን እውቀት አካፍሉ።
7. 1 ጴጥሮስ 4፡19 የተነገረው ቆራጥ ምክር ምንድ ነው? አሁን ለእኛ ምን ይጠቅማል?
8. ከዛሬ ጥናት ምን ተማራችሁ? **እናካፍል።**

# ጥናት አስራ አንድ

## 1ጴጥሮስ 5፡1-6 ለክርስቲያን መሪ አገልጋዮች የተሰጠ ምክር

**ዓላማ፡-** ክርስቲያን መሪ አገልጋዮች ምንም እንኳን መከራ ውስጥ ቢያልፉም ኃይለኛው እግዚአብሔር በመጨረሻ ክብር እንደሚሰጣቸው በመገንዘብ የተሰጣቸውን አደራ እነደሚገባ መወጣት እንዳለባቸው ማሳሰብ።

**መግቢያ፡-** ክርስቲያን መሪ ለምን መከራ ይቀበላል? በመከራ ውስጥስ ምን ኃላፊነት አለበት? እያገለገለ ያለውስ መንጋ የማን መንጋ ነው? እነዚህ ጥያቄዎች በዚህ ጥናት ይመለሳሉ። ጽድቅ በሌለበት ዓለም ጽድቅ ለምታውጅ ለክርስቶስ አካል መሪዎች ተሹመዋል። በመጀመሪያዎቹ መቶዎች ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን መምራት እጅግ ከባድ ነበር ምክንያቱም ስደትና መከራ ህይወት እስከማጣት ድረስ ያደርስ ነበር። በርግጥ ስለ ክርስትና ሞትና መከራ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች አሁንም አለ። ቢሆንም ግን በዚህ ምድር ሰውነታችን ቢጎዳም ክብር ያለውን ዓለም በማሰብ ማንኛውንም ልዩ ልዩ መከራ እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች እንዲንቀበል ያበራታተናል። እነዚህንና የመሳሰሉ ነገሮችን በዚህ ጥናት እንነጋገራለ።

### 1. 1ጴጥሮስ 5፡1-3 የአገልጋዮች ኃላፊነት በመከራ ውስጥ፡-

**1ጴጥሮስ 5፡**1 **እንግዲህ** ብሎ ይጀምራል። ይህ ቃል ምዕራፍ 5 ከምዕ 4 ሀሳብ ጋር የተያያዘ መልእክት መሆኑን ይነግረናል። ማለትም **ሐዋርያው ጴጥሮስ** ስለ መከራቸው ብዙ ከተናገረ በኋላ እርሱም የመከራው ተካፋይ መሆኑን ለመንገር እየተዘጋጀ ነው። "እኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ **የክርስቶስም መከራ ምስክር** ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤..."። የዮሐንስ ወንጌል 21፡15 ይነበብ። ለሐዋርያው ጴጥሮስ ጌታ መንጋውን አደራ ሰጥቶታል። አንዳንዶች ሐዋ ጴጥሮስም ያገለግል የነበረ አጥቢያ ቤ/ክ ነበረው ይላሉ። ቢሆንም ባይሆንም የመጋቢዎችና የመሪዎች አገልጋይ እንደሆነ ግልጽ ነው። እርሱም አብሮ የሚቀበል መከራ እንዳለ ያረጋግጣል። **የክርስቶስም መከራ ምስክር፡- ማቴ 26፡58** እንደሚነግረን ሐዋ ጴጥሮስ የክርስቶስን መከራና ክብር ያየ የዓይን ምስክር ነበር። ያም ብቻ ሳይሆን የጌታን መገለጥ ክብር ከሚጠብቁ

አማኞች መካከል እርሱም ይመደባል። መልዕክቱን በሚጽፍበት ወቅት በመከራ ውስጥ ነበር። በተቃራኒ ደግሞ በርግጥ የማቴ 17፡1-8 እንደሚያሳየን ጴጥሮስ በተራራ ላይ ስለጌታ ከአባቱ ስለተነገሩ ነገሮችና ክብር ምስክር ነበር። 1 ዮሐ 1፡1-3 ሐዋርያት የዓይን ምስክር ስለመሆናቸው ተጨማሪ ማብራሪያ አለው።የሐዋርያት ሥራ ከምዕራፍ 1-12 ስለ ጴጥሮስ መከራ መቀበል በግልጽ ማየት ይቻላል። **ጴጥሮስ መከራ ብቻ ሳይሆን እየነገረን ያለው ለአማኞች ከጌታ ዘንድ ክብርም እየጠበቀን መሆኑን ያስረግጣል።**

**መሪ አገልጋይ ማን ነው? እንዴትስ መምራት አለበት?** ይህ ክፍል በርግጥ በዋናነት የሚያመለክተን በተለይም ቤ/ክንቷን የሚያስተዳድሩና የጌታን ቃል የሚያስተምሩ መሪዎችን ቢሆንም በጌታ ቤት ሁለትና ሶስት ሰዎችንም የምንመራ ከሆነን መሪዎች መሆናችንን መዘንጋት የለብንም። አደራ አለብን። ታዲያ እንዴት እንምራቸው የሚለውን ጥያቄ ከዚህ ቀጥሎ ይመልሳል። መልሱ **1ጴጥሮስ 5፡2 ተጽፏል ሀ. በመጠበቅ፡-** “ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ”። መጠበቅ የሚለው ቃል እነደባለ ሞያተኛ (ተቀጣሪ) እረኛ ሳይሆን እንደ እውነተኛ የበጎች እረኛ ሥራና አገልግሎት መሆን ያለበት ኃላፊነት ነው(ዮሐ 10፡10-12፣ሐዋ 20፡28)። መንጋው የመሪው እንዳልሆነም ማወቅ አለበት ወይም አለብን። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው መሪ ህይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ እረኛ ማለት ነው። **ለ. በፈቃደኝነት፡-** “ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን…”፥ የዳነ ሰው ሲያገለግል ባለ ማወቅ አንዳንድ ጊዜ በማግሮምሮም ደስተኛ ሳይሆን ማገልገል ይችል ይሆናል። ቢሆንም ግን ጌታ ይህንን አገልግሎት አይፈልግም። እነዚህ መሪዎች ምንም እንኳን ስደትና መከራ ቢበዛባቸውም በፈቃደኝነትና በትልቅ ደስታ እንዲያገልግሉ ይጠይቃቸዋል። **ሐ. ጥቅም ፍለጋ መሆን የለበትም- ሐሰተኛ አስተማሪዎች ጥቅም ለማግኘት ብለው እንደሚያገለግሉ በጊዜውም ይሁን አሁንም የታወቀ ነው። ነገር ግን መሆን ያለበት** “በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት፤” ነው። መንፈሳዊ አገልግሎት የዚህ ዓለም የተለያዩ ዓይነት መከራዎች ያለበት ቢሆንም ከጥቅም ጋር መያያዝ የለበትም በደስታ እንጂ ግዳጅ እንደሆነም ማሰብ የለብንም። **መ. በምሳሌነት ማገልገል፡-** “ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ

ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤"። መሪ አገልጋዮች መንጋው (የምንመራቸው ጥቅትም ሰዎች) የሚከተለን መሆኑን አውቀን ምሳሌ መሆን አለብን። በመከራም ጭምር ምሳሌ መሆን ማለት ነው፡፡ ኃጢአት ባበላሸው ዓለም ስላለን ኃጢአትን ስንቃወም መከራ በመሪዎች ላይ መነሳቱ አይቀርም። ቢሆንም ግን ለሌሎች ጽድቅን ማሳየትና መኖር አለብን። ከመከራ ለማምለጥም በመጥፎ ምሳሌ መታየት የለብንም። "ወንድሞች ሆይ፥ እኔን የምትመስሉ ሁኑ፥ እኛም እንደ ምሳሌ እንደምንሆንላችሁ፥ እንዲሁ የሚመላለሱትን ተመልከቱ" (ፊል 3፡17) ። እነ ሐዋሪያው ጳውሎስ መሪዎች ስለሆኑ ብዙ መከራ ይደርስባቸው ነበር። ሐዋሪያው ጴጥሮስም እንደዚሁ ነበር።

**በምንድ ነው ምሳሌ የሚንሆነው?** **ሀ.** በቃል፡-ንግግርን ያመለክታል ወይም አንደበትን መጠበቅ **ለ.** በኑሮ፡-በቤት ፤በትምህርትና በምንሰራበት ቦታ ሁሉ የተቀደሰ ኑሮ መኖር **ሐ.** በፍቅር፡- በመከራ ውስጥ ሰዎችን እንደ ጌታ ቃል መውደድን ያሳያል **መ.** በእምነት፡- ጌታ ከሁሉ ያድናል ብሎ ባልተቀላቀለ ትምክህት በመከራ ውስጥ ማለፍ ኔ **ሠ.** በንጽሕና ሁሉ፡- ማንም ስለ ክርስትና የሚከሰን ነገር መኖር የለበትም ( 1ጢሞ 4፡11-12)። ጌታ ሁሉ ቦታ ስላለ ለአማኞችም ይሁን ላላመኑ የማመን እድል እንዲያገኙና እንዲበርቱ በየእለቱ ጥሩ ተግባር የተሞላ ምሳሌ ያለበት ህይወት መኖር አለብን።

## 2. 1ጴጥሮስ 5፡4-7 የአገልጋዮች ተስፋ በመከራ ውስጥ

መከራ ምን ተስፋና ውጤት አለው? ለክርስቲያኖች እግዚአብሔር ካዘጋጃቸው አክሊሎች ለምሳሌ **ከማይጠፋው፣ ከድል፣ ከጽድቅ፣ ከክብር፣ከህይወት፣ከወርቅ** ወዘተ **አንዱ እዚህ ቦታ ይገኛል። ቁ.4 ላይ** "የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ **የማያልፈውን የክብርን አክሊል** ትቀበላላችሁ" ይላል። ጌታችን የእረኞች ማለትም የእረኞችም ይሁን የበጎችም እረኛ ሲመጣ ዘላለማዊ የሆነውን ሽልማት በጊዜያዊ መከራ ምትክ እንደሚሰጠን ያረጋግጣል። ስለዚህ በጎቹ በራሱ በበጎቹ ባለቤት የተሰጠ አደራ ነው።

በአራቱም ቁጥሮች ስለ መሪዎች ወይም መጋቢዎች ከተናገረ በኋላ ቁ.5 ላይ በጣም አጭር በሆነ መስመር **"እንዲሁም፥ ጐበዞች ሆይ፥ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤..."** ጎልማሶች ወይም ወጣቶች ቀጥሎ ያለውን የመሪነት አገልግሎት የሚቀበሉ ስለሆኑ ለመሪዎች በፍቅር እየተገዙ በጊዜው ከነበረው ዓለማዊ ጥበብ ለመንፈሳዊ ነገር ትኩረት እንዲሰጡ ይጠይቃቸዋል። በርግጥ 1ጴጥሮስ 2፡13-3፡7 ስለ መገዛት ብዙ አስተምሯል። 1ጴጥ 2፡13 "ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ"። **ሁላችሁም ትህትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፡-** "... **ሁላችሁም** እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ **ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥** እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።" ይህ ክፍል ደግሞ ሁሉ አማኝ (መሪዎችም ይሁን ተከታዮች በተለይም ወጣት ክርስቲያኖች) እርስ በርስ ስለ ጌታ ትሁት እንዲንሆኑ ይጠይቃል። በዚህ ምክንያት በመከራ ውስጥ የሚያልፉበትን ጸጋ ጌታ ይሰጣል። ጸጋውም መከራ ውስጥ ለማለፍ ጉልበት ይሆናል።

### 3. 1ጴጥሮስ 5፡6-7 መከራ ይኑር እንጂ ለክርስቲያን ከፍታ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው የሚሆነው፡-

**"**6 እንግዲህ **በጊዜው** ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ፤" ይህ ክፍል ብዙ ትምህርት ያስተምራል። ለምሳሌ ጌታ ከሁሉም ከአሳዳችም በላይ ኃይለኛ መሆኑን ሰው ሁሉ አውቆ በምንም መከራ ውስጥ ቢያልፍ ለጊዜው እንደሆነ ማወቅ አለበት። በጊዜው የሚለው ቃል ደግሞ እዚህ ምድር ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሚያበቃ ወይንም ወደ ጌታ ዘላለማዊ መንግስት የማይዘልቅ መሆኑን ያሳያል። ጌታም ለጊዜው መከራ ተቀብሏል። **ኃላፊነት የሚወስድ አለ** "7 እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።" በመከራ የሚጨነቁት ሁሉ በኃይለኛው በጌታ ለይ ላይ ሸክማቸውን እንዲጥሉ ይነግራቸዋል። ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ጌታ በጊዜው ከነበሩት ነገሥታትም የበላይ እንደሆነ እየነገራቸው ይገኛል። ስለዚህ ጌታ ሁልጊዜ ለራሱ ዓላማ ካልሆነ ልጆቹን መከራ ውስጥ አያስገባም።

## መደምደሚያ

የጌታ ቃል  እርሱ ጌታ አደራ ለሰጠን መንጋ መልካም ምሳሌዎችና ስለ ክርስቶስም መከራ የምንቀበል መሆን እንዳለብን ይነግረናል።  አገልግሎታችንም በደስታና በፈቃደኝነት መሆን አለበት። በግድና በመጨነቅ ባለማወቅ መሆን የለበትም። በዚህ ምድር ላይ ክርስትና መከራ የበዛበት ቢሆንም በመጨረሻ ክብር እንዳለው ይህ ክፍል ያረጋግጣል። የአገልጋዮች ተስፋ ከሚያልፉበት መከራ በላይ እንደሆነ በተጨማሪም ያሳውቃል። ለክርስቲያን ከፍታ የጊዜ ጉዳይ ብቻ እንጂ አብሮ የሚቆይ ዘላለማዊ አይደለም።የሁሉም እረኛ ዋጋ ይዞ በሙላት ይገለጣል።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. **1ጴጥሮስ 5፡1-3 በማንበብ** ሐዋርያው ጴጥሮስ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ? አዎን ካላችሁ ሐዋ 15፡1-7 ከዮሐ 21፡15 በማንበብ በአጭሩ ተወያዩ።
2. 1ጴጥሮስ 5፡1 ከ1 ዮሐ 1፡1-3 ጋር ምን ግንኙነት አለው።
3. በዚህ ጥናት "…**ሁላችሁም**…" የሚል ቃል የተጠቀሰው ቁጥር ስንት ላይ ነው? ምንና ማንን ለማመልከት ይመስላችሁሃል?
4. የዮሐ 10፡10-12 እና ሐዋ 20፡28  በማንበብ ለትክክለኛ እረኛ የተሰጠውን ኃላፊነት ለቡድኑ ተናገሩ
5. 1ጴጥሮስ 5፡2 በማንበብ ለአገልጋይ ስንት ኃላፊነቶች ተሰጥቶ ይገኛል? እነዚህ ነገሮች እንዴት ማገልገል እንዳለበት ያሳያል። ጌታ ትሁት ስለሆነ ምን አደረገ?
6. **1ጴጥሮስ 5፡4-7 በማንበብ በልባችሁ የቀረውን ነገር ተወያዩ።**
7. መሪ ማን ነው? ምን እንዲሆን ይጠበቅበታል?
8. **ዛሬ የተማርኩትን ላካፍላችሁ?**

# ጥናት አሥራ ሁለት

## የንባብ ክፍል 1ጴጥሮስ 5፡8-14

## በመከራና በሰይጣን ሥራ ለይ በእምነት መጽናት፡- አማኝ ተስፋ እንዳለው ክርስቲያን መኖር አለበት

**ዓላማ**፡- ክርስቲያን  በመከራ ውስጥ ተስፋ እንዳለውና ክብር እንደሚጠብቀው በማወቅ በጌታ እየታመነ ሰይጣንን በመቃወም ጥቂት ጊዜ ማለፍ እንዳለበት ማሳሰብ።

**መግቢያ፡-** ዳግመኛ የተወለደ ሰው መከራ ውስጥ ሲያልፍ ሰይጣን ያንን መከራ እንደ ምክንያት በመጠቀም በህይወቱ የተለያዩ መንፈሳዊ ጥያቄዎችን ሊያስነሳ ይችላል። አማኝ ምንም እንኳን ህይወቱን በጽድቅ ለመያዝ በሚያደርገው ጥረት በኃጢአትና በሰይጣን ምክንያት መከራ ቢመጣበትም የዚህን ምድር ጊዜያዊ ልዩ ልዩ መከራዎችን ሲያልፍ ትልቅ ዘላለማዊ ክብር በእግዚአብሔር  ዘንድ  ይጠብቀዋል። ስለዚህ በእምነት መጽናት ይጠበቅበታል። ይህ ጥናት ይህንን ሀሳብ ያብራራል።

### 1. 1ጴጥሮስ 5፡8-9፡-  በመከራ ውስጥ የሚያልፉ አማኞች የሰይጣን ክፉ ሴራ ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው

በዚህ ክፍል በግልጽ ሰይጣን የአማኞች ባለጋራ እንደሆነ ይናገራል (ተቃዋሚ ወይም ጠላት ማለት ነው) ። በተጨማሪም ለማብራራት የተጠቀመው አውሬ አንበሳ ነው (ጉልበታም ሆኖ ሊበላ ይዞራል)። ሐዋ ጴጥሮስ በመልዕክቱ ብዙ ስለ  ሰይጣን ወይም ስለ ዲያብሎስ  አልተናገረም ነገር ግን የተለያዩ ነገሮችን በመጠቀም የሰውን ሀሳብ መበከልና ማስፈራራት ከዚያም እምነት በማጣት ራስን ከሰጡ ወዳልታሰበበት ውድቀት ሊመራ እንደሚችል አይክድም። ሰይጣን **በእግዚአብሔር ማንነት ላይም ጥያቄ  ሊያስነሳ  ይችላል።** ሰይጣን ከሁሉ በላይ የሰውን ሀሳብ መበከል ሥራው ነው። መከራ መቀበል አያስፈልጋችሁም ልል ይችላል። የጌታ ሰዎች መከራ እንዴት ይገጥማቸዋል ብሎም ሊያታልል ይችላል (ኢዮ 1፡9-11)። አማኝ ከሆንክ ብልጥግና ያስፈልግሃል እያለ ልሸነግልና ሐሰተኛ ስለሆነ ሐሰት ሊናገር ይችላል። አማኞችን ካታለላቸው በኋላ ዓላማውም ከጌታ መለየት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስን በክብር፣ በረሃብ፣በብልጥግናና በእግዚአብሔር ማንነት ላይ ጥያቄዎችን በማስነሳት ለመፈተን ብዙ ሞክሯል (ማቴ 4፡1-11)። በእግዚአብሔር ኃይል ላይም ጥያቄ ለመፍጠር ጥረት አድርጓል። እውቀታችንን፣ፈቃዳችንንና ስሜታችንን ካስገዛን በተቻለው መጠን የእግዚአብሔርን ቃል መጥቀስና ማጣመም ይጀምራል።

ስለዚህ **ሐዋርያው ጴጥሮስ** በመጠን ኑሩ ንቁም ይላል፥ **"ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤"**። ዲያብሎስ በግሪክ ጠላት ማለት ሲሆን ማንነታችንን ከሰጠነው ሊያጠቃን ይችላል። ስለዚህ ጸንተን መቃወም አለብን። ማስፈራራትም ዋናው ሥራው ነው። ግን ጌታ የእርሱንም አፍ የሚዘጋ ኃይል አለው። "14 ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን [ጠላት] ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና" (2ቆሮ 11፡13-14)። በመጠን መኖር አንዱ ሰይጣንን መቃወምያ መንገድ ነው።ለሥጋዊ ነገሮች ከመጠን በላይ መጨነቅ ለሰይጣን በር መክፈት ነው።

1ጴጥ5፡9 ላይ ሌሎችም ስለ ክርስትና መከራ እየተቀበሉ እንዳሉ ይናገራል ማለትም የጴጥሮስ መልዕክት ተደራስያን ብቻ አልነበረም መከራ ይቀበሉ የነበሩ። አሁንም ቢሆን መከራ ብንቀበል እኛ ብቻ አይደለንም። "9 **በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ** በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።" በብሉይ ኪዳን ዮሴፍ፣ዳንኤልና ጓደኞቹ ሌሎችም ስለ ጽድቅ መከራን አልፈው ታርከን ለውጠዋል። በዕብራውያን መልእክት ምዕራፍ 11 የተጠቀሱ የእምነት አባቶች ለዚህ ምሳሌ ናቸው። በዚህ ዘመንም መከራ ውስጥ እያለፉ ያሉ ብዙ ህያዋን ወንድሞችና እህቶች አሉ።

## 2. 1ጴጥ 5፡10-11 በመከራ ውስጥ በጌታ ጸጋ የሚያልፍ ክብር የሚጠብቀው ሕዝብ (መከራ ጊዜያዊ ነው)

**"10 በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል ያበረታችሁማል። 11 ለእርሱ ክብርና ኃይል እስከዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን።"**

ይህ ክፍል እንግዲህ ሰይጣን ወይም ከሳሽና ጠላት (ዘካ 3፡1፣ኢዮ 1፡1-6 ረዕይ 12፡10) በመከራ ውስጥ ክፉ ሴራ ቢኖረውም የጌታ ጸጋ ከዚያ በላይ መሆኑን ያሳያል። ይህንን ጸጋ ለማግኘት አማኝ በጌታ መታመን አለበት። ከመከራ ጌታ ያወጣኛል ብሎ በእግዚአብሔር መታመን ሌላው ሰይጣንን የምንቃወምበት መንገድ ነው።

ይሁንና **ግን መከራው እስከ መቼ ነው?** ይህ ተደጋግሞ የተመለሰ መልስ ነው። መልሱም ለጥቂት ጊዜ ነው። ጥቂት ጊዜ ስንት ጊዜ ወይም ምን ያህል ነው? ጴጥሮስ በሁለተኛው መልዕክቱ 3፡8 እንዲህ ይላል " በጌታ ዘንድ አንድ **ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን** እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ" በማለት ለጌታ እኛ ብዙ ልንል የምንችላቸው ነገሮች ጥቂት ሊሆኑ እንደሚችሉ ይናገራል። ስለዚህ መከራው በጸጋው ሲታለፍ የማይገመት ጥቂት ጊዜ ነው። በዚህ ምድር ሊያበቃ የሚችል ወይም ባይሆን በጌታ መንግስት የማይኖር ነገር ነው። ሌላው በዚህ ክፍል መሰመር ያለበት ነጥብ እኛ መከራ ውስጥ እያለፈን ያለን አማኞች **የዘላለም ክብር የሚጠብቀን የጌታ ልጆች ነን** "በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ <u>ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል ያበረታችሁማል</u> (5፡10)።" ራሱ እግዚአብሔር በጸጋው እስከዚያው ቀን ድረስ በመከራ ያጸናል፣ያበረታል። ስለዚህ ይህን ሁሉ ጸጋ ለሰጠን ጌታ **"ለእርሱ ክብርና ኃይል እስከዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን"።**

## 3. 1ጴጥሮስ 5፡ 12 -14 የሕይወት ልምድ ምክርና ሰላምታ በመከራ ውስጥ ላሉት

ይህን መልእክት በተጻፈበት ወቅት ሐዋርያው ጴጥሮስ ከሰላሳ ዓመታት በላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አገልግሏል። ከዚህም በመነሳት እርሱ ያለፈበት ጸጋ እውነተኛ የጌታ ጸጋ መሆኑን ያረጋግጥላቸዋል። በመደምደሚያም ሁለት አገልጋዮችን በዚህ መከራ በጽናት በመታመን አብረውት እያገለገሉ የነበሩትን ያነሳቸዋል፤ ስልዋኖስ (ሲላስ) እና ማርቆስ (የማርቆስን ወንጌልን የጻፈው) ናቸው። ከላይ እንደተጠቀሰው ሐዋርያው ጴጥሮስ ማርቆስ ወንጌሉን እንዲጽፍ በብዙ የረዳው ወንጌላዊ እንደሆነ ይታመነል። በመግቢያ እንደተጠቀሰው **"በባቢሎን ያለች ቤተ ክርስቲያን" የሚለው**

**በሮም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሌላ መጠሪያ ስሟ ነው ብለው ብዙዎች ይስማማሉ። ባቢሎን በብሉይ ኪዳን እንጂ በአዲስ ኪዳን አይታወቅም፤ጴጥሮስም በዚያ ስለመኖሩ ምንም መረጃ የለም። በመጨረሻም** የፍቅር ሰላምታ ትልቅ በመከራው ውስጥ ለሚያልፉ መነቃቂያና ማበራተቻ መንገድ ነው። ስለዚህ የፍቅር ሰላምታ እንዲለዋወጡ ይመክራቸዋል። እኛም መከራ ውስጥ ያለን አማኞች እርስ በእርስ መፈቃቀርና መዋደድ ቢኖር መከራውን አብሮ እያተጋፈጡ ለማለፍ ያስችላል። እርስ በርስም መረዳዳት እንችላለን።

## መደምደሚያ

1ጴጥሮስ 5፡8-14 ማንም አማኝ የሚያልፍበትን መከራ ለዲያብሎስ መጠቀሚያ መሳሪያ ማድረግ የለበትም። ሰይጣንም በየቀኑ ስለሚዞር ሊያጠቃው ይችላል። የእግዚአሔር ጸጋ በመከራ ውስጥ በጠላት ሥራ በእምነት በመጽናት ተስፋ እንዳለው ክርስቲያን በመኖር ማለፍ እንደምንችል ይናገራል። በመጨረሻም ትልቅ ክብር አለው። ስለ ህይወት ደህንነት የምንቀበለው መከራ ጊዜያዊ እንደሆነ እርግጠኞች መሆን አለብን። ካለፉት አባቶችና ህያዋንም ከሆኑ አማኞች ሕይወት ልምድ መማርም ትልቅ ብርታት ይሰጣል።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. **1ጴጥሮስ 5፡8-9** በማንበብ ያገኛችሁትን እውቀት  አካፍሉ። በዚህ ክፍል በምሳሌ የተጠቀመው አውሬ ምንድ ነው? ምንን ያመለክታል? ይህ አውሬ በመከራ ውስጥ ካሉት አማኞች ጋር ምን ይሰራል?
2. በማቴ 4፡1-11 ከተጠቀሰው በክርስቶስ ላይ ሰይጣን ሊያመጣ የሞከራቸው ፈተናዎች ምን ምን ነበሩ? ከፈተናዎቹስ ምን እንማራለን?
3. ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለ ሰይጣን ከተናገረ በኋላ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ መናገር መጀመሩ ለምን ይመስላችሁሃል? በመጠን መኖርስ ሰይጣንን ከመቃም ጋር ምን ይገናኛል?

4. 1ጴጥሮስ 5፡9 **<u>“በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ..”</u> የሚል መልዕክት ይብራራ? በመከራ ውስጥስ ላሉት አማኞች ምን ይጠቅማል?**
5. 1ጴጥሮስ 5፡10 ላይ “በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ **ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ** የጸጋ ሁሉ አምላክ **ለጥቂት ጊዜ** መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል ያበረታችሁማል።” በዚህ ቁጥር “በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ” ብሎ መጥቀስ ለምን አስፈለገ? ጥቂት ጊዜስ ምን ያህል ጊዜ ነው?
6. የእምነት አባቶች ስለ ክርስትና ጽድቅ መከራ የተቀበሉትን አንስታችሁ ተወያዩ
   - **ዳንኤልና ጓደኞች (ትንቢተ ዳንኤል)**
   - **ጌታ ኢየሱስ**
   - **ሐዋርያት**
   - **ዕብራዊያን 11**
   - **ሌሎች ህያዋን**
7. ከነዚህ ሰዎች ህይወትና አገልግሎት ምን ተማርን?
8. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርን?
9. አጠቃላይ ከጴጥሮስ መልእክት ምን ተማራችሁ? እርስ በእርስ በመረዳዳት በሚቀጠለው ቀን አብሮ ማእድ የመቁረስ ጊዜ ቢኖራችሁ ህብረታችሁን ያጠነክራል። በአንድ ሰው ላይ ሸክም እንዳይበዛ እንላለን።

ማስታወሻ**፡-** ስለ ጥናቱ ያላችሁን ማንኛውንም አስተየየት በመሪያችሁ በኩል ንገሩን (ወይንም ቢሮ ትምህርት ክፍል በመምጣትም ይሁን በመደወል የልባችሁን ማካፈል ትችላላችሁ)። ጌታ ከእናንተ ጋር አብረን እንድንሰራ ስለ ሰጠን ጸጋ ስሙ ይመስገን።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ